ስብሓት ፡ ለአምላክ ።

ከኢትዮጵያ ፡ ወንጌላዊት ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

፲፱፻፸፫ ፡ ዓ. ም.

በብርሃንና ፡ ስላም ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ፡
ታተመ ፤ ፰ ፡ ፭ ፡ ፵፫ ፡ ቁ. ፯፻፭፰ ፡

FROM THE LIBRARY OF
BIBLE LANDS MUSEUM
BML

አንቀጽ ።	ገጽ፡
ሀ ። የእግዚአብሔር ፡ ግርማና ፡ ክብር ፤	
፩ ፡ የእግዚአብሔር፡ምስጋና ፡	፩
፪ ፡ የእግዚአብሔር፡ክብር፡ በክርስቶስ ፡	፬
ለ።የቤተ፡ክርስቲያን፡በዓላት፤	
፫ ፡ የክርስቶስ ፡ መምጣት ፡	፯፩
፬ ፡ ልደቱ ፡	፴፪
፭ ፡ ሕማማቱ ፡	፵
፮ ፡ ትንሣኤው ፡	፵፬
፯ ፡ በዓለ ፡ ኀምሳ ፡	፶፬
፰ ፡ ዕርገቱ ፡	፶፰
፱ ፡ ጸራቅሊጦስ ፡	፷፪
፲ ፡ ሥላሴ ፡	፷፯
፲፩ ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡	፸፮
፲፪ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡	፸፱
ሐ።ቤተ፡ክርስቲያንና፡ጸጋ፡ መሥሪያ ፤	
፲፫ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡	፹፭
፲፬ ፡ ቃሉ ፡	፹፯
፲፭ ፡ ጥምቀት ፡	፺፭

ገጽ ፡

ፀ ፡ ቅዱስ ፡ ቀርበን ፡ ፻፸፱

ፁ ፡ የጉባኤው ፡ ስብሰባ ፡ ፻፹፭

ፂ ፡ ጋብቻ ፡ ፻፻፹፪

ፃ ፡ የወንጌል ፡ ሥራ ፡ ፻፻፹፯

መ ። የክርስትና፡አካሄድ ፡

ፅ ፡ መጠራትና ፡ ብርሃን ፡ ፻፺

መቀበል ፡

ፆ ፡ ንስሐና ፡ መመለስ ፡ ፪፻፲፪

ፇ ፡ ጸጋውን ፡ መቀበል ፡ ፪፻፴፩

ፈ ፡ የምእመን ፡ ደስታ ፡ ፪፻፵፬

ፉ ፡ ጸሎት ፡ ፫፻፯

ፊ ፡ የምእመን፡አካሄድ ፡ ፫፻፴፭

ሠ።የጧትና ፡ የማታ ፡

መገሠፅራት ፡ ፫፻፺፩

ረ ። ቤትና ፡ አገር ፡ ፫፻፺፱

ሰ።የሕፃናት፡መገሠፅራት ፡ ፬፻፲

ሸ ።ሁለተኛ ፡ መምጣቱና ፡

ፍርዱ ፡ ፬፻፲፭

ቀ።የዘላለም ፡ ብፅዕና ፡ ፬፻፴፭

በ።ናፍቆሚ ፡ ፬፻፵፭

ሀ ።

ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ቅኞር ፡ ፻፱

ሁሉም ፡ ሩጠው ፡ ፻፻፵፰

ሦማዕና ፡ ፲፰

ለ ።

ለትልቅ ፡ ሥራህ ፡ ለንፍ ፡ ኑኝ ፡ ፻፶፱

ላምላክ ፡ በሰማይ ፡ ፪

ለአምላካችን ፡ በሰማይ ፡ ፰፯

ለአምላክ ፡ ዘምሩ ፡ ፫

ለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ፲፯

ለእስራኤል ፡ አምላክ ፡ ፻፲፪

ለየሱስ ፡ ሰም ፡ ይሁን ፡ ስብሓት ፡ ፲፩

ለደስታ ፡ ቀን ፡ ፳፭

ላምላክ ፡ በሰማይ ፡ ቀኙ ፡ ፳፱

ላንተ ፡ ስብሓት ፡ ይሁን ፡ ፯

ሌት ፡ አበራ ፡ የጽድቅ ፡ ፀሐይ ፡ ፪፻፵፱

ልመናዬን ፡ በሰ ፡ ስማኝ ፡ ፭

ለሰርግ ፡ ሲጠራ ፡ ፻፲፫

ልባችሁ ፡ አይደንግጥ ፡ ፪፻፴፱

ልዑል ፡ አምላክ ፡ ፻፹፯

ልጆቹን ፡ ለማከማቸት ፡ ፪፻፻፱ ለ

ሐ ።

ሕዝቦች ፡ ሆይ ፡ ቍጥር ፡ ፭
ሕይወቴን ፡ ለመጥሁልህ ፡ ፻፱፫
ሕግ ፡ ፈረደብን ፡ ፻፲፱
ሕፃን ፡ ተወለደ ፡ በዚህ ፡ ሌት ፡ ፹
ሕፃን ፡ ተወልዶዋል ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ፭፻፱
ሕፃን ፡ ተወልዶልናል ፡ ፱፻፫

መ ።

መለከት ፡ ንፋ ፡ ፪፻፲፭
መንጋህን ፡ ስታሰ ግራ ፡ ፪፻፲
መንገድ ፡ አብጅ ፡ ለጌታ ፡ ፻፯
መንገደኛ ፡ መናኝ ፡ ሁንያለው ፡ ፪፻፫፱
መንግሥቱን ፡ ሕገቡን ፡ ፪፻፶፱
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ ፫፹
መድኃኒት ፡ ተገኘ ፡ ከአብ ፡ ፭፫
መድኃኒት ፡ ተገኝልን ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፲፱፭
መድኃኒቱን ፡ ብዎ ፡ ፲፫፯
መድኃኒቴ ፡ ወደኔ ፡ ና ፡ ፲፻፱
መድኃኔ ፡ ተቀበለኝ ፡ ፪፻፫
መጣሁ ፡ ወደ ፡ መስቀልህ ፡ ፲፻፭
ምስጉን ፡ ጊዜ ፡ ፭፻፫

ሰ ።

ሰባኪው ፡ አለ ፡ ፲፻፯
ሳይመለስ ፡ ይዘገያል ፡ ፪፻፲፭

ሰለ ፡ ሕይወት ፡ ዋና ፡ ጥቅም ፡ ቍጥር ፡ ፪፻፵፱
ሥሉጥ ፡ አምላክ ፡ ፹፯
ሰመለከት ፡ ያን ፡ ድንቅ ፡ መስቀል ፡ ፵፯
ሰግልኝ ፡ የሱስ ፡ ጸሎቴን ፡ ፻፲፪
ሰማን ፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አሁን ፡ ፪፻፲፫
ስትጨነቅ ፡ ብለህ ፡ ፪፻፴፭
ስብሓት ፡ ስብሓት ፡ ስብሓት ፡ ፴፯
ስብሓት ፡ ክብረትም ፡ ፪፻፶፪
ስንሰበሰብ ፡ በኤድን ፡ ፪፻፵፱ ፡ ፱
ስንት ፡ ብፅዕና ፡ ታደለ ፡ ፲፫፱
ስንንገዝ ፡ በደረቅ ፡ አገር ፡ ፪፻፫፪

ቀ ።

ቃልህን ፡ አ ቅዱስ ፡ ጌታ ፡ ፻፯
ቅዱስ ፡ ሕዝብ ፡ ፲፲፯
ቅዱስ ፡ ሥላሴ ፡ ፲፭
ቅዱስ ፡ ቃሉን ፡ የሚሰሙ ፡ ፲፫
ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ፯
ቀሚን ፡ ሆነች ፡ ፲፱፱

በ ።

በልብህ ፡ ያለውን ፡ ትካዜህን ፡ ፪፻፱፪
በመላ ፡ ዓለም ፡ ፲፻፯
በመስቀል ፡ ሞተ ፡ ፶፩
በመቃብር ፡ ተኛ ፡ ፭፫

በመድኃኔዓለም ፡ ለአመንት ፡ ቀኖጥር ፡ ፪፻፷፱
በምን ፡ መሠረት ፡ ሠርተሃል ፡ ፪፻፸፩
በ ማያት ። ፪፻፸፪
በቀረበ ፡ ጊዜ ፡ የፈሲክ ፡ በዓል ። ፪፻፸፬
በቤተ ፡ ልሔም ፡ በረት ። ፯፫
በብፁዓን ፡ መናርያ ፡ ፪፻፸፱
በተስፋ ፡ ስቀርበው ። ፫፻፱
በአምላክ ፡ ተመርተን ። ፯፪
በአፋችሁም ። ፯፱
በእውነት ፡ ባንተ ፡ ያመንው ። ፫፻፭
በክርስቶስ ፡ ቀኖስል ። ፪፻፸፯
በክርስቶስ ፡ ደም ፡ የስጠኸን ። ፫፭
ቤክርስቶስ ፡ ምክር ፡ የማይገኝ ፡ ፪፻፸፱
በዓለሙ ፡ እንደ ፡ ቤቴ ። ፪፻፯
በዙፋኑ ፡ ፊት ፡ ድንው ። ፪፻፹፫
በዚህ ፡ በእንሳድንቴ ። ፪፻፸፫
በዚያ ፡ ዓለም ፡ ንዘን ፡ ፪፻፫፭
በየሱስ ፡ ፊት ፡ ይቆማሉ ። ፹፭
በሞንቅም ፡ በደስታም ። ፪፫፯
በጸጋው ፡ እግዚአብሔር ። ፲፱
በጽዮን ፡ ደንጊያ ። ፪፭፯
ባርክን ፡ ሙበቀን ። ፪፻፹፭
ብሩህ ። በሓይ ። ፪፻፸፯
ብርሃን ፡ በሌት ፡ እንደሚዘልቅ ። ፹፱

ቸ
ቸሉ ፡ መድኃኔቴ ፡ ፬፻፯
ቸሉ ፡ ጠባቂ ፡ ምሬን ፡ ፮፭፯
ኀ ።
ኀዘን ፡ ወይም ፡ ደስታ ፡ ፪፻፭፯
ኀዘንተኛን ፡ ደጸናናው ፡ ፪፻፭፱
ኃጢአተኞችን ፡ እንዲያድን ፡ ፬፻፯
ኃጢአቴ ፡ ያሳዝነኛል ፡ ፮፭፯
ነ።
ነቢያት ፡ ያዩልን ፡ ቀን ፡ ፲፯
ነፍስ ፡ ለእምላክሽ ፡ ተሰጪ ፡ ፪፻፹፫
ኑ ፡ ውላችን ፡ ፵፱
ኑ ፡ አክብሩት ፡ ጌታን ፡ ፵፱
ኑ ፡ እላንት ፡ ለዎች ፡ ፲
ኑ ፡ ደከሞች ፡ ውላችሁ ፡ ፪፻፱
ና ፡ ቸር ፡ መሐሪ ፡ ፪፻፭

ና ፣ ጌታ ፣ የሱስ ፣ ቅጥር ፣ ፻፴፱
ንቁ ፣ ቁሙ ፣ ለየሱስ ፣ ፻፵፩

አ

እሁን ፣ መሽትሞልና ፣ ፻፻፵፯
አልመለስ ፣ ብልሙ ፣ አይሁድ ፣ ፻፫
አልረካውም ፣ ያንን ፣ ጊዜ ፣ ፵
አስት ፣ ቢፈርስም ፣ ፻፻፻
አመልግኑት ፣ ክርስቶስን ፣ ፻፫
አምላካችንን ፣ እናመሰግን ፣ ፻፻፲፱
አምላክሞ ፣ ጸዳል ፣ ፻፻፳፭
አምላክህ - ስፍርድ ፣ ፻፻፳
አምላክ ፣ ሁለቱን ፣ ፻፲፱
አምላክ ፣ ሆይ ፣ የነፍሴን ፣ ጕድለት ፣ ፻፻፲፯
አምላክ ፣ በምሕረቱ ፣ ብዛት ፣ ፻፶፭
አምላክ ፣ በመንፈስህ ፣ ፻፲፱
እምላክን ፣ አክብሩ ፣ ፵
አምላክ ፣ ከእናንት ፣ ዘንድ ፣ ይውን ፣ ፻፻፲፯
አምላክ ፣ የኔ ፣ እረኛ ፣ ፲፭
አምላክ ፣ ይመስገን ፣ ፻፫
አምላክ ፣ የፈላገው ፣ ፻፭
አምላኬ ፣ ወዳንት ፣ ፻፲፭
አምላኬ ፣ ፊትህን ፣ አትሰውርብኝ ፣ ፻፻፻
አምላክ ፣ ፍቅር ፣ ነው ፣ ፻፲፯
አምባችን ፣ አምላካችን ፣ ፻፲፲

አባታችን ፣ ጌታችን ፣ ሆይ ፣ ቅጥር ፣ ፻፻፻
አባትን ፣ ስብሐ ፣ ፹
አቤቱ ፣ በጸጋህ ፣ ፻፱
አርነት ፣ ወጣሁኝ ፣ ፻፲፫
አንተን ፣ የሱስ ፣ ሆይ ፣ እሻለሁ ፣ ፻፫
አንተ ፣ እውነተኛ ፣ አምላክ ፣ ፻፫
አንድ ፣ ቀን ፣ በአምላክ ፣ አደራሽ ፣ ፻፻፻፯
አንድ ፣ ቀን ፣ ላይናችን ፣ ፻፻፲፱
አንድ ፣ ወዳጅ ፣ ፲፯
አንድ ፣ ጥሩ ፣ ስም ፣ ፻፻፫ ሀ
ኦያለሁ ፣ የሱስ ፣ ስሮንትህን ፣ ፫፻
አዲሳ ፣ ያልተወለደ ፣ ፻፵፫
አዳም ፣ በውድቀቱ ፣ ፻፲
አዳኜ ፣ ደሙ ፣ ፈሰስ ፣ ፻፲
እነሆ ፣ ሳሕዝብ ፣ ዛፊ ፣ ፻፲
እናምናለን ፣ በአባት ፣ ፫፻
እኔ ፣ የሱስን ፣ ለማየት ፣ ፻፷
እንሰብሰብ ፣ በሥይን ፣ ፻፻፻፱ ለ
እንደ ፣ ቅርምዝ ፣ ፻፸፫
እንደ ፣ እናት ፣ ፻፻፻
እንዲት ፣ የሚገርም ፣ ነው ፣ ፻፸፰
እንዲት ፣ ጸጋ ፣ ነው ፣ ፻፹፱
እወድሃለሁ ፣ የሱስ ፣ ሆይ ፣ ፻፫
እፈልንቃለሁኝ ፣ ፻፻፻፯

አ ፡ መንፈስ ፡ሕይወትን፡ላገኝ ፡ ቍጥር ፡ ፻፲
አ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ና ፡ ወደኔ ፡ ፻፳፭
አ ፡ መድኃኒታችን ፡ ፱
አ ፡ ርኅሩኅ ፡ አምላክ ፡ ፻፱፻፰
አ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ፲፫፫
አ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ ፻፳
አ ፡ ቸር ፡ መድኃኒቴ ፡ ፻፲
አ ፡ ንፍሴ ፡ አሁን ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ፡ ፻፲፭፭
አ ፡ አምላኬ ፡ ፻፴፯
አ ፡ አምላኬ ፡ አንተ ፡ ፱፻፻፱፱
አ ፡ የሱስ ፡ ቃልህ ፡ ዐንትዋል ፡ ፶፱፫
አ ፡ የሱስ ፡ ቅዱስ ፡ እጅህ ፡ ፱፻፵፭፯
አ ፡ የሱስ ፡ አመሰቅ ፡ ፻፳፭
አ ፡ የሱስ ፡ አምላኬ ፡ ፲፻፶፱
አ ፡ የሱስ ፡ ከኔ ፡ ተባበር ፡ ፱፻፻፲
አ ፡ የሱስ ፡ የሕይወት ፡ ውኃ ፡ ፻፸፭
አ ፡ የሱስ ፡ ያንተን ፡ ልጆች ፡ ፲፯፭
አ ፡ የሱስ ፡ ጌታዬ ፡ ፻
አ ፡ ያምላክ ፡ በግ ፡ ፵፭
አ ፡ ደስታ ፡ ቀን ፡ ፻፻፲፯
አ ፡ ጌታ ፡ ሠይ ፡ ፱፻፲፯
አ ፡ ግሩም ፡ ጊዜ ፡ ፳፭

ከ

አ ፡ ግሩም ፡ ጠቅላይ ፡ ጌታ ፡ ቍጥር ፡ ፱
ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከውኃ ፡ ፶፯
ከሰማይ ፡ ማን ፡ ወረደ ፡ ፱፻፻፶፯
ከአምላካችን ፡ ማን ፡ ይበልጥ ፡ ፻፵፱
ከአምላክ ፡ ዘንድ ፡ በመገናኘት ፡ ፻፱፱
ከአምላክ ፡ ፍርድ ፡ ልታድንን ፡ ፶፱፭
ከክበደ ፡ ኃጢአቴ ፡ ፻፴፯
ከክንቱ ፡ ዓለም ፡ ፱፻፻፵፱
ከዕለታት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ፱፻፻፵፱
ከዘላለም ፡ የወጣ ፡ ፱፻፻፵፭
ከዚህ ፡ መሄዴ ፡ ፱፻፻፲፯
ከየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጽድቅ ፡ ፻፻፱
ከምላክ ፡ የራቅንውን ፡ ኃጥኣን ፡ ፶
ከንቺ ፡ ላይ ፡ ይበራልና ፡ ፱፻፻፻፫
ክርስቶስ ፡ ሕያው ፡ ሆነ ፡ ፶፯
ክርስቶስ ፡ የኛ ፡ መመኪያ ፡ ፱፻፻፵
ክርስቶስ ፡ ዛሬ ፡ ተነሥትዋል ፡ ፻፱
ክቡር ፡ መድኃኒቴ ፡ ፻፻፱

ወ

ወንድሞቼ ፡ እንንሣ ፡ ፻፲፱
ወንጌል ፡ የሚለውን ፡ ስምቼ ፡ ፻፻፱
ወደ ፡ መቅደስ ፡ ተራሮች ፡ ፻፲፭

ወይ ፡ ቅዱስ ፡ ቅኵስ ፡ ቅጥር ፡ ፻፯
ወየ ፡ ከበረው ፡ አገር ፡ በሳይ ፡ ፪፻፫፫
ወዳምላክ ፡ ልብ ፡ ፻፻፫
ወይኛ ፡ የሱስ ፡ ሲመጣ ፡ ፪፻፻፱ ሀ
ወይ ፡ ጸጋ ፡ ዙፋን ፡ ፻፷፯
ወይት ፡ አመልጣለሁ ፡ ፪፻፷፫
ወዳንተ ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡ ፪፻፲፩

ዐ

ዐልት ፡ ቢፈርስም ፡ ተራራ ፡ ፯
ዕዳ ፡ ተከፍሎ ፡ ፷፯

የ

የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ አየሁ ፡ ፻፷፫
የልብህ ፡ በር ፡ ፻፸፯
የልደት ፡ ግታ ፡ ፴፯
የልደት ፡ ቀን ፡ ሲመጣ ፡ ፴፫
የመስቀል ፡ ውርደት ፡ ፵፫
የሚሰማ ፡ ሁሉ ፡ ፻፷፯
የማይነገር ፡ ነው ፡ ፭፯
የምስራችን ፡ ፻፻፯
የሩሳሌም ፡ እልል ፡ በዪ ፡ ፳
የስይጣንን ፡ መኖሪያ ፡ ፻፵፯
የሱስ ፡ ሆን ፡ ተስፋዬ ፡ ፻፫
የሱስ ፡ ሆይ ፡ ሕፃናትን ፡ ፶፯
የሱስ ፡ ሆይ ፡ ምራን ፡ ፻፲፭

የሱስ ፡ ሆይ፡በዚህ፡በምድር፡ቀጥር፡ ፻፻፯
የሱስ ፡ ሆይ ፡ አትለፍብኝ ፡ ፻፻፫
የሱስ ፡ ሆይ ፡ የልቤ ፡ ተስፋ ፡ ፻፵
የሱስ ፡ ሆይ ፡ ደንተ ፡ ሕማማት ፡ ፵፱
የሱስ ፡ ሆይ ፡ ጤና ፡ ሰላምም ፡ ፴፱
የሱስ ፡ ለዓለም ፡ ፴፯
የሱስ ፡ ልቤን ፡ ውሰድልኝ ፡ ፻፶፯
የሱስ ፡ መድኃኒትህ ፡ ፻፳፭
የሱስ ፡ ሲጠራህ ፡ ፻፳፱ለ
የሱስ ፡ በመስቀል ፡ ሞተልን ፡ ፶፫
የሱስ ፡ በመስቀል ፡ ሳለ ፡ ፵፯
የሱስ ፡ በሚመራኝ ፡ መንገድ ፡ ፻፲፯
የሱስ ፡ ባንተ ፡ ድኜ ፡ ፪፻፫
የሱስ ፡ ኃጢአቴን ፡ ፻፵፫
የሱስ ፡ እንደወደደኝ ፡ ፪፻፻፭
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ራሱ ፡ ፻፲፯
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ፵፭
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወንድም ፡ ፪፻፳፯
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡ ፯፯
የሱስ ፡ ጫደ ፡ ሐይህበት ፡ ፪፻፲፱
የሱስ ፡ ያስፈልገኛል ፡ ፫፫
የተመረጡ ፡ በስማያት ፡ ፪፻፻፯
የተሰቀለው ፡ መድኃኔ ፡ ፻፻ ለ

የተናቀ ፡ ስውም ፡ ቊጥር ፡ ፱፭፭
የኔ ፡ ነህ ፡ ኦ የሱስ ፡ ፱፱
የክበረ ፡ ቤት ፡ በሰማይ ፡ ፱፫
የአምላክ ፡ ቃል ፡ ፱፲፭
የአምላክን ፡ ውስጥ ፡ ሁሉ ፡ ፱፭፱
የክበረ ፡ ቤቱ ፡ በላይ ፡ ፱፱፱፭
የክርስቶስ ፡ ያምላካችን ፡ ሞት ፡ ፺፱
የየሩሳሌም ፡ ልጆች ፡ ፱፱፶፭
የየሱስ ፡ መልካሙን ፡ ድምጽ ፡ ፱፶፭
የየሱስ ፡ ስም ፡ ያጸናናል ፡ ፺፭
የየሱስ ፡ ልብ ፡ ተከፈተልህ ፡ ፱፭፯
የደስታ ፡ ሌት ፡ ፭፱
የደስታ ፡ ዘመን ፡ ሁንዋል ፡ ፭፭
የጥንት ፡ አምባ ፡ ፱፶፱
የጌታ ፡ መለከት ፡ ሲነፋ ፡ ፱፱፫
የጸሎት ፡ ስዓት ፡ ፱፱፯
ያለደስታ ፡ ስናር ፡ ፱፭፭
ያልደረስሁበት ፡ አክሊል ፡ ፱፱፭፱
ያምላክ ፡ ሕዝብ ፡ የጽዮን ፡ ወገን ፡ ፱፱፻፯
ያምላክ ፡ በግ ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ፺፭
ያምላካችን ፡ ታናሽ ፡ ጭፍራ ፡ ፱፱፱፯
ያምላክ ፡ ጸጋ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ፱፲፱
ያምላክን ፡ ጸጋ ፡ አላውቅም ፡ ፱፲፯
ያብ ፡ ሥምረት ፡ ፻፭

ያባትህ ፡ እቅፍ ፡ ቊጥር ፡ ፱፻፭
ያ. ኤዲስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ፱፱፻፭
ያ. ታላቅ ፡ ሐኪም ፡ ፱፶፱
ያች ፡ ታናሽ ፡ መንጋ ፡ ፱፱፻፹፭
ያንትን ፡ ስላም ፡ ፱፱፲፯
ያን ፡ ክቡር ፡ ዕንቁ ፡ ፱፫፱
ያ. ኤዲስ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ፱፱፻፭
ያፈስልህልን ፡ ፡ ደምህን ፡ ፫፯
ደመራኛል ፡ ይመራኛል ፡ ፭፱
የ.ሐንስ ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ፱፻

ደ ።

ደስ ፡ በይ ፡ ነፍሴ ፡ ሆይ ፡ ፱፱፭፱
ደስ ፡ ይበለኝ ፡ ፱፱፻
ደስ ፡ እንዲሰን ፡ ይገባናል ፡ ፲፱
ደካሞች ፡ ኑ, ፱፱፲፭
ድል ፡ ነሥተሃል ፡ ፭፱

ገ ።

ገስግሶ ፡ ሲያልፍ ፡ ቀናችን ፡ ፱፱፻፭
ገብተናል ፡ በአምላክ ፡ መቅደስ ፡ ፱፭
ጊዜ ፡ ይመሻል ፡ ፱፱፻፫
ጌታ ፡ ከላይ ፡ ተገልጥዋል ፡ ፭፭
ጌታን ፡ ስንከተል ፡ ፱፱፻፹
ጌታ ፡ ከሞት ፡ ተነሥተዋል ፡ ፭

ጌታ ፡ የሱስን ፡ ናፈቅሁኝ ፡ ቸኮር ፡ ፻፸፫
ጌታ ፡ ፍቅርህን ፡ ፻፸፮

ጠ ።

ጢስኛ ፡ ስደተኛ ፡ ፻፸፰፻፭

ፈ ።

ፈለስግው ፡ ሌሊትም ፡ ፻፸፰፻፱

ጸ ።

ጸውልን ፡ እንዳበባ ፡ ፻፹
ጸጋህን ፡ ስጠኝ ፡ ፻፹፩
ጽናት ፡ በየሱስ ፡ እጅች ፡ ፻፹፪

ፀ ።

ፀሓይ ፡ ወጣ ፡ ፻፲፯

ፈ ።

ፈርዎን ፡ የእስራኤል ፡ ፻፲፰
ፍርዳዳችንን ፡ የወሰድኸው ፡ ፻፲፩
ፍቅር ፡ ላንተ ፡ የሱስ ፡ ፻፲፲፩
ፍቅር ፡ ታጋሽ ፡ ናት ፡ ፻፲፳፮

መ ግ ለ ጫ ።

S.T. Sions Toner

Am. በአሜሪካን ፡ ሚስዮን ፡ የታተመ ፡ የዜማ ፡ መጽሐፍ ።

ልዩ ፡ ዜማ ፡ ለገጹ ፡ መገመራት ፡ በተለየ ፡ የታተመ ፡ ዜማ ።

መ ታ ረ ሚ ያ ።

ገጽ ፡	ስሕተት ፡	የታረመ ፡
6	S.T. 215. Am. 120	S.T. 215
41	Am. 14	Am.149
95	Am. 13	Am.136
96	ኋላኛው ፡	ኋለኛው ፡
117	S.T. 53. 4. Am. 131	S.T. 53 4.
134	S.T. 678	S.T. 677
179	እናመሰግን ፡	እናመስግን ፡
192	የሕወት ፡	የሕይወት ፡

መታረሚያ ።

195	አታዝጋ ፣	አትዝጋ ፣
201	የሚመጡ ፣	የምትመጡ ፣
227	ተቀብልህልኝ ፣	ተቀበልህልኝ ፣
257	S.T. 598. 105.	S.T. 598. 105 Am. 87.
277	ውዳጅ ፣	ወዳጅ ፣
281	Am. 85.	S.T. 438. Am. 86
336	S.T. 308.	S.T. 308 Am. 116.
425	ስታርግ	ስታደርግ ፣
457	ተቀበለው ፣	ተቀብለው ፣

ምስጋና ።

፩

S. T. 19 Am. 139

፩ ፡ ሕዝቦች፡ሆይ፡ደስ፡ይበላችሁ፡
አምላክን ፡ አመስግኑ ።
የቆማችሁ ፡ በኪዳን ፡
በአንድነት ፡ ቀረቡ ።
ቀረቡ ፡ በእልልታ ፡
ዘምሩ ፡ ለቸር ፡ ጌታ ።

፪ ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ የፈጠረን ፡
ልጆቹን ፡ የጠራን ፡
የጠፉትንም ፡ ያዳነ ፡
እስካሁን ፡ ያቆመን ።
እርሱ ፡ ከሰማይ ፡ ደስታ ፡
አደራጅልን ፡ ስፍራ ።

፫ ፡ ዘምሩለት ፡ በበሮቹ ፡
ወደሱት ፡ በመቅደሱ ።

ካገር ፡ ሁሉ ፡ ተከማቹ ፡
ላባታችን ፡ ስገዱ ።
ርኅሩኅ ፡ ሁኖ ፡ ይጸናል ፡
እስከ ፡ ሞት ፡ ይመራናል ።

O. E.

፪

S. T. 57 Am. 183

፩ ፤ ላምላክ ፡ በሰማይ ፡ ቀኙ ፡
ሕዝቦች ፡ ሁሉ ፡ ይስገዱ ።
ድምፅ ፡ ያለበት ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡
ያመስግን ፡ በመቅደሱ ።
፪ ፤ በእጁ ፡ የፈጠረው ፡
እጅግ ፡ ግሩምና ፡ መልካም ፡ ነው ።
ከዘላለም ፡ ያሳየው ፡
ተገልጦልን ፡ ግርማው ።
፫ ፤ ከአምላክ ፡ ላስታረቀን ፡
ከጥፋት ፡ ለነጠቀን ፡
እንዳበት ፡ ላሞገሰን ፡
እንዘምር ፡ ሁሉ ፡ ቀን ፡

፬ ፤ ፍጥረቱ ፡ በመላዋ ፡
ስብሓት ፡ ታቅርብ ፡ ለጌታ ።
ነፍሴም ፡ ደግሞ ፡ በደስታ ፡
ታመስግን ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

O. E.

፫

S. T. 50 Am. 155

፩ ፤ ለአምላክ ፡ ዘምሩ ፡
በእርሱ ፡ ደስ ፡ ይበለን ።
በታላቅ ፡ ፍቅሩ ፡
ግሩም ፡ ውለታ ፡ ሠራልን ።
ከእናት ፡ ማሕፀን ፡
በምሕረት ፡ እስካሁን ፡
ወትሮ ፡ ሰጠብቀን ፡
ሠራልን ፡ መልካሙን ።
፪ ፤ የጸጋ ፡ አምላክን ፡
ወትሮ ፡ እንድንፈራ ፡
መንፈሱንም ፡ ይስጠን ፡
በእርሱም ፡ እንመራ ።

የምሕረት ፡ አምላክም ፡
ይስጠነ ፡ ምሕረቱን ።
እስከ ፡ ዘላለምም ፡
ከእኛ ፡ ጋር ፡ ይሁን ።

ፒ ፡ ሰርክ ፡ እናመስግንህ ፡
አ፡አብ፡አ፡ወልድ፡አ፡መንፈስ።
ዘላለም ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡
አ ፡ አንተ ፡ ሥሉስ ፡ ቅዱስ ።
ለቅዱስ ፡ ሥላሴ ፡
ለሥስቱ ፡ አካላት ፡
እናቅርብ ፡ ውዳሴ ፡
እናቅርብም ፡ ስብሓት ።

ረስቱን ።

ዕ

S. T. 58

ጀ ፡ አ ፡ ግሩም ፡ ጠቅላይ ፡ ጌታ ፡
ሁሉን ፡ የሚገዛ ፡
ለአንተ ፡ ይሁን ፡ ምስጋና ።

አትፍረድብን ፡
ምሕረት ፡ አድርግልን ፡
ቅዱስ ፡ መንግድህን ፡ አሳየን ።
ሁሉ ፡ ቀን ፡ አምላክን ፡
ከመላእክቱ ፡ ማኅበር ፡
በደስታ ፡ እናክብር ።

ፀ ፡ ለፈጣሪ ፡ ክብረት ፡
እልል ፡ በል ፡ አ ፡ ፍጥረት ፡
በልዩ ፡ ድምፅ ፡ ዘምርለት ።
በእሳት ፡ የጋልሽ ፡
ብርሃን ፡ የመላብሽ ፡
አንቺ ፡ አብሪ ፡ ለፈጣሪሽ ።
አእላፍት ፡ ከከቦች ፡
ጨረቃም ፡ ይዘምሩ ፡
ሥልጣኑን ፡ ያሳዩ ።

ፒ ፡ ነፍሴ ፡ ሆይ ፡ ለጌታ ፡
አቅርቢ ፡ ምስጋና ፡
ቤቱን ፡ ጉበትሽ ፡ በእልልታ ።

ይስገዱለት ፡ ሁሉ ፡
ለክብሩ ፡ ይኑሩ ፡
በቅናት ፡ ግዛቱን ፡ ያስፉ ።
ባለም ፡ ላይ ፡ በሰማይ ፡
በዘላለም ፡ ዘመን ፡
ይመስገን ፡ ጌታችን ።

O. E.

፰

S. T. 215 Am. 120

፩ ፤ ልመናዬን ፡ ስለ ፡ ሰማኝ ፡
አምላክን ፡ ልወድስ ፡ ነኝ ።
ረጆች ፡ ሁሉ ፡ ሲርቁብኝ ፡
አምላክ ፡ ኃይል ፡ ረድኤት ፡ ሆነኝ ።
ክፉን ፡ ሁሉ ፡ ሊያሸንፍ ፡
ሕዝቡን ፡ በሰልፉ ፡ ሊደግፍ ።
፪ ፤ በጤና ፡ ወይ ፡ በሞት ፡ ጊዜ ፡
አለኝ ፡ ተስፋ ፡ በምላኬ ።
እርሱ ፡ ረድቶኛል ፡ በጭንቁ ፡

አሁን ፡ ደስ ፡ ይላል ፡ ልቤ ።
ስለዚህ ፡ እርሱን ፡ ላመስግን ፡
እርሱን ፡ ለማገልገል ፡ ልፍጠን ።
፫ ፤ ልዑል ፡ አምላክ ፡ ሁን ፡ ኃይል
ላችን ፡
ሕዝብህን ፡ ከሞት ፡ አድን ።
ማኅበርህን ፡ በዓለም ፡ አግንን ፡
ጠብቅ ፡ ግዛ ፡ ርስትህን ።
ተከባከበን ፡ በምድር ፡
አልቀን ፡ በሰማይ ፡ ክብር ፡

O. E.

፱

(ኢሳ ፡ ፮ ፡ ፫ ፡) S. T. 668

፩ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡
ስብሓት ፡ ላንት ፡ በሰማይ ፡
ለምትኖር ፡
ይገባናል ፡ ምስጋናህን ፡ ልንዘምር ፡
በልባችን ፡ ቅዱስ ፡ ቃልህ ፡ ይደር ።
፪ ፤ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡
እግዚአብሔር ፡

ነዋሪ ፡ አምላክ ፡ በሰማይ ፡ በምድር ፡
የምታቀል ፡ የኃጢአትን ፡ ቀንበር ፡
በምሕረትህ ፡ ስጠን ፡ ሰላም ፡ ፍቅር ።

፫ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱስ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡
መሐሪ ፡ አምላክ ፡ በደልን ፡ የሚምር ፡
ስንለምንህ ፡ በኤድን ፡ ገነት ፡ ልንኖር ፡
አካፍለን ፡ ክብዐ-ግን ፡ ማጎበር ።

ቁ. ፱ ።

፯

ልዩ ፡ ዜማ ፡ ፩ ።

ላንተ ፡ ስብሐት ፡ ይሁን ፡
አ ፡ ሥሉስ ፡ አምላክ ፡
በጌታ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ።
በልጅህ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ስለ ፡ ሰጠኸን ፡ ሁሉ ፡
አንተን ፡ እናመሰግናለን ።
አሜን ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

የእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ በክርስቶስ ፡

፯

God Save the Queen S. T. 74

፩ ፡ አምላክን ፡ አክብሩ ፡
እሙን ፡ ነው ፡ ምክሩ ፡
ይስፋ ፡ ክብሩ ።
በኃይሉ ፡ ነግሥዋል ፡
ጸጋን ፡ ለግሶልናል ።
እንዴት ፡ ያስደንቃል ፡
ታላቅ ፡ ፍቅሩ ።

፪ ፡ ተዋረደ ፡ ለሰው ፡
ጽዋውም ፡ መረረው ፡
ሲቀበለው ።
መድኃኒቱም ፡ ሲሞት ፡
መላእክት ፡ አደነቁት ፡
መሰቀሉም ፡ ሕይወት ፡
ሊሰጠን ፡ ነው ።

፫ ፡ ምሕረቱ ፡ ታላቅ ፡ ነው ።
ሊያመሰግነው ፡
አይበቃም ፡ ሰው ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ በሰማይ ፡
ግርማውን ፡ በግልጥ ፡ ስናይ ፡
ምስጋናው ፡ የቀላይ ፡
ምሳሌ ፡ ነው ። ፠
፬ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ታች ፡ አውን ፡
ጀምሩ ፡ አዲሱን ፡
ድንቅ ፡ መዝሙሩን ። ፠
ያምላክ ፡ ነው ፡ መንግሥትም ፡
ኃይል ፡ ገናንነትም ፡
እስክ ፡ ዘላለምም ፡
ለርሱ ፡ ይሁን ። ፠

ረስቲን ፡

S. T. 58

፩ ፡ አ ፡ መድኃኒታችን ፡ አ ፡ የክ
ብር ፡ ንጉሥ ፡
አ ፡ ፈጣሪ ፡ ጠባቂያችንም ፡
ዘመን ፡ ሲለዋወጥ ፡ አንተ ፡
ሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡

ለዘላለም ፡ አትለወጥም ። ፠
ስምህን ፡ ላመስግን ። ፠
ነፍስ ፡ ያላቸው ፡ ሁሉ ፡
ክብርህን ፡ ይዘምራሉ ። ፠
፪ ፡ አ ፡ የቂሰልህልን ፡ ርኅሩኅ ፡
ንጉሣችን ፡
ስለ ፡ በጎችህ ፡ የተሰቀልኸው ፡
አንተ ፡ ትሰጣለህ ፡ ኃይል ፡
በድካማችን ። ፠
ምስጋናችንን ፡ ተቀበለው ። ፠
አ ፡ መድኅን ፡ ተመስገን ። ፠
ውዳሴ ፡ ስብሓትም ፡
ይሁንልህ ፡ ለዘላለም ። ፠

S. T. 59 Am. 178

፩ ፡ ኑ ፡ እናንት ፡ ሰዎች ፡
ጌታን ፡ እናመስግን ፡
አብራችሁም ፡ ልጆች ፡
አመስግኑ ፡ ፍቅሩን ፡
አክብሩ ፡ ጸጋውን ።
፪ ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡
በግርማ ፡ ሲመላ ፡
የሰማይ ፡ ክብር ፡
ትዩ ፡ በትሕትና ፡
ስለኛ ፡ ተገዛ ።
፫ ፡ ያን ፡ ደዊያችን ፡
እርሱ ፡ ተሸከመ ፡
ኃጢአትን ፡ ሞትን ፡
ለኛ ፡ አሸነፈ ፡
ሰላሙን ፡ ሰጠን ።

፬ ፡ እኛን ፡ ሊበጀን ፡
ንጹሐ ፡ ቂሰለ ።
ለርሱ ፡ ሊዋጀን ፡
እጅግ ፡ ተጋደለ ፡
በመስቀሉ ፡ ሞተ ።
፭ ፡ ሊያዘጋጀን ፡
መ·ሽራው ፡ ልንሆን ፡
ሞገስ ፡ ሊሰጠን ፡
በስሙ ፡ ስናምን ፡
ጽድቁን ፡ ተላብሰን ።
፮ ፡ በቃል ፡ በሥራ ፡
የሱስን ፡ ለማክበር ፡
በሞቀ ፡ ደሴታ ፡
ስለ ፡ አምላክ ፡ ፍቅር ፡
በመዝመ·ር ፡ እናክብር ።

ሎንዳል ።

O. E.

፲፩

Am. 151. S. T. 81

፩ ፡ ለየሱስ ፡ ስም ፡ ይሁን ፡
ስብሓት ፡
ኑ ፡ ለርሱ ፡ ስገዱለት ፡
መሥዋዕትንም ፡ አቅርቡለት ።
ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡
ንጉሠ ፡ ስብሓት ።
፪ ፤ በደሙ ፡ የተገዛችሁ ፡
ከሞትም ፡ የዳናችሁ ፡
ስገዱለት ፡ ላነጻችሁ ።
ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡
ልዑል ፡ ጌታችሁ ።
፫ ፤ ለርሱ ፡ ይሁን ፡ ምስጋናችን ፡
ለልዑል ፡ አምላካችን ፡
እናንግሠው ፡ በልባችን ።

ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡
መድኃኒታችን ።

፲፪

S. T. 4 Am. 113

፩ ፤ ደስ ፡ እንዲለን ፡ ይገባናል ፡
ባገኘነው ፡ ድንቅ ፡ ነገር ።
አምላክ ፡ አሁን ፡ ይምረናል ፡
ፍርዳችን ፡ ሞት ፡ የነበር ።
ሊምረን ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡
የሚለን ፡ ቃሉን ፡ ሰደደ ።
ይህም ፡ ደስታችን ፡ ሆነ ።
፪ ፤ የሰይጣን ፡ ባርያ ፡ ነበርሁኝ ፡
መዳኔም ፡ አልተቻለም ።
በኃጢአቴ ፡ ታሰርሁኝ ፡
ልጠፋ ፡ ለዘላለም ።
ወደ ፡ ሲኦል ፡ እሳት ፡ ልወርድ ፡

በገዛ ፡ ሕሊናዬ ፡ ፍርድ ፡
እንደሚገባኝ ፡ ሆነ ።

፫ ፡ ተስፋ ፡ስቄርጥም፡ ከጥፋት ፡
መዳን ፡ ስላልታየልኝ ፡
አምላክ ፡ በምሕረቱ ፡ ብዛት ፡
በአባት ፡ ፍቅር ፡ አየኝ ።
በኃጢአቱ ፡ ታስሬ ፡
ሳለሁ ፡ ተሰጠኝ ፡ ያባቴ ፡
ቸርነትና ፡ ፍቅር ።

፬ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ፡
እራራላቸዋለሁ ።
እኒያን ፡ ምስኪን ፡ አስሮች ፡
ልልጀ ፡ እሰጣለሁ ።
በደሙ ፡ ከዘላለም ፡ ሞት ፡
ሊያድናቸው ፡ አዘዝሁት ፡
ሊሆንላቸውም ፡ ሕይወት ።

፭ ፡ አባቴም ፡ እንደ ፡ ፈቀደ ፡
ወልድ ፡ ታዘዘ ፡ በፍቅሩ ።

ከሰውም ፡ ሥጋ ፡ ተዋሐደ ፡
ሲሰወርበት ፡ ክብሩ ።
ሕግ ፡ በኔ ፡ እንደ ፡ ፈረደ ፡
ሊሞት ፡ በመስቀል ፡ ወረደ ፡
ከሞቴም ፡ ሊያወጣኝ ።

፯ ፡ ከግቡ ፡ ፍርዴም ፡ እንድድን ፡
ሕይወቴን ፡ ለወጠልኝ ፡
የከበረም ፡ የየሱስ ፡ ደም ፡
በመስቀል ፡ ፈሰሰልኝ ።
ሲሞት ፡ አወጣኝ ፡ ከፍርዴ ፡
ሆነልኝም ፡ አማላጄ ፡
ባባቴም ፡ ፊት ፡ ቆመልኝ ።

፰ ፡ ከዚህም ፡ ዓለም ፡ መከረ ፡
ወዳባቴ ፡ ወጣልኝ ።
ለጭንቀቴም ፡ የሚራራ ፡
ጸራቅሊጦስ ፡ መጣልኝ ።
ለንስሓ ፡ ይጠራኛል ፡
በእውነትም ፡ ይመራኛል ፡

በልቤም ፡ አደረልኝ ።

፰ ፡ ለአምላክ ፡ ውዳሴ ፡ ይሁን ፡
ምስጋናም ፡ ለዘላለም ።
ይህን ፡ ረድኤት ፡ ከሰጠን ፡
በአምላክ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።
ኃጢአትና ፡ ሞት ፡ መርገምም ፡
በክርስቶስ ፡ ሞት ፡ አስወገደ ።
ማን ፡ ነው ፡ የሚያስኰንን ፡
ረስቲን ፡

Praise Him
Praise Him
223

፲፫

Am. 127.

፩ ፡ አመስግኑት ፡ ክርስቶስን ፡
መድኃኒታችን ፡
ዘምሩ ፡ ፍቅሩንም ፡ አስታውቁ ።
አመስግኑት ፡ ክርስቶስን ፡ የጥንት ፡
አምባችን ፡
ክብርም ፡ ሁሉ ፡ ይሁንለት ፡ ለርሱ ።

የሱስ ፡ ነውና ፡ ቸሩ ፡ ጠባቂያችን ።
በክንዱም ፡ ይሸከመናል ፡ እርሱ ።
አመስግኑት ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡
መድኃኒታችን ፡
አመስግኑ ፡ የሱስን ፡ አክብሩ ።

፪ ፡ አመስግኑት ፡ ክርስቶስን ፡
መድኃኒታችን ፡
ለኛ ፡ ሲልም ፡ ደሙን ፡ አፈሰሰ ።
አምላካችን ፡ ነው ፡ ተስፋችን ፡
መጠጊያችን ፡
ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡ ሞትን ፡ ያሸነፈ ።
ስግዱለት ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ንጉሣችን ፡
ታላቅ ፡ ፍቅሩን ፡ ለኛ ፡ የገለጠ ።
አመስግኑት ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡
መድኃኒታችን ፡
ክብር ፡ ይሁን ፡ ከሞት ፡ ላዳነን ።

፫ ፡ አመስግኑት ፡ ክርስቶስን ፡
መድኃኒታችን ፡

አዲስ ፡ ቅዱስ ፡ ቅኔ ፡ ተቀኙለት ።
የሱስ ፡ ክቡ ፡ ይንገሥልን ፡ በልባችን ፡
ይንገሥ ፡ ይንገሥ ፡ ለርሱ ፡
ይሁን ፡ ስብሓት ።
ሊመጣ ነው ፡ ነቢይ ፡ ሊቀ ፡ ካህናችን ፡
ክብር ፡ ኃይልም ፡ ለርሱ ፡ ሊሆንለት ።
አመስግኑት ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡
መድኃኒታችን ፡
አመስግኑ ፡ የሱስን ፡ አክብሩ ።

ፕ፬

S. T. 92 Am. 175

፩ ፡ ጸውልጎ ፡ እንደ ፡ አበባ ፡
ሲቀር ፡ የዓለም ፡ ተስፋ ፡
ውኃ ፡ ፈልቆ ፡ በበረሃ ፡
ለተጸማ ፡
ነፍሱን ፡ የሚያረካ ።

፪ ፡ ክርስቶስ ፡ ፍቅሩን ፡ እያሳየን ፡
የሕይወት ፡ ምንጭ ፡ ሆነልን ።

በደሙ ፡ የሚያድነን ፡
ለነፍሳችን ፡
ሀብቱን ፡ አቀረበልን ።

፫ ፡ በዓለም ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ብቻ ፡
ከጭንቀት ፡ የሚረዳ ።
ሊሰጥ ፡ ለኃጥኣን ፡ ይቅርታ ፡
ምሉ ፡ ጸጋ ፡
ኑዛዜ ፡ ለሚገባ ።

፬ ፡ ከየሱስ ፡ ነው ፡ ብርሃን ፡ እውነት ፡
ሆነልን ፡ መንገድ ፡ ሕይወት ።
የፈለገው ፡ ያገኘዋል ፡
ይሰጠዋል ፡
ለለመነው ፡ በእምነት ።

፭ ፡ በመላ ፡ ዕድሚያችን ፡ ቀን ፡
እጆቹን ፡ ዘረጋልን ።
ገና ፡ እኛን ፡ ይታገሣል ፡
ይጠረናል ፡
እምነትን ፡ አጸናልን ።

፯ ፡ በጎ ፡ እረኛ ፡ ሁንዋል ፡
የገዴለውን ፡ ይመላል ።
በወንጌል ፡ በቅዱስ ፡ እራት ፡
ሰጠን ፡ ብፅዓት ።
ርኅሩኅ ፡ ሆኖ ፡ ይኖራል ።

፯ ፤ ከሱነኔ ፡ ሊያድነን ፡
ስንት ፡ ውለታ ፡ ዋለልን ።
ድል ፡ ይሰጣል ፡ በጦርነት ፡
በቸርነት ፡
ሆነልን ፡ ጤና ፡ ሕይወት ።

፰ ፤ እንደ ፡ አባት ፡ አሳድረን ፡
ጸጋህን ፡ አቅርብልን ።
ሰላምን ፡ ስጥ ፡ ለችጉር ፡ ነፍስ ፡
ለኛ ፡ ለግስ ፡
ይህ ፡ ጉዞ ፡ እስኪጠረስ ።

፱ ፤ በሚደርስብን ፡ መከራ ፡
ሆንህልን ፡ ረድኤት ፡ ተስፋ ።
በጭንቅ ፡ በሞት ፡ አሳልፈህ ፡

በመንግሥትህ ፡
ብዕዕናን ፡ ትሰጣለህ ።

O. E.

፲፩

S. T. 89. Am. 113.

፩ ፡ ለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ልትዋጅ ፡
ሥጋችንን ፡ የለበስኽ ፡
ተስፋችንን ፡ ልታዘጋጅ ፡
አ ፡ የሱስ ፡ ሞትን ፡ ቀመስኽ ።
ያላንተ ፡ ግን ፡ በጠፋን ፡
ሲያል ፡ ተከፈተብን ፡
ሞትም ፡ ርስታችን ፡ ነበር ።

፪ ፤ አንተም ፡ ስታይ ፡ የኛን ፡ ጕዳት ፡
በፍቅር ፡ ራራህልን ፤
ልታድነንም ፡ ኩኖፋት ፡
ወዳለም ፡ ወረድህልን ።
ከአንክ ፡ ሞትና ፡ ሕማም ፡
የእግዚአብሔር ፡ ሰላም ፡
አ ፡ የሱስ ፡ ተገኘልን ።

፫ ፤ በትሩፋትህ ፡ አምነን ፡
ወዳምላክ ፡ ስንመጣ ፡
ምሉ ፡ ይቅርታ ፡ ሰጠኸን ፡
በሕግ ፡ እንዳንቀጣ ።
እኛም ፡ ይህን ፡ ተቀብለን ፡
በቅዱስ ፡ ቃልህ ፡ ታምነን ፡
ከሞት ፡ እንድናለን ።

፬ ፤ ቸር ፡ ወንድማችን ፡ አንተ ፡ ነህ ፤
እንዴት ፡ አክብረኸናል ።
ዘላለም ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ነህ ፡
ሁሉንም ፡ ሰጥተኸናል ።
የዓለም ፡ ስድብና ፡ ጥል ፡
ከቶ ፡ ሊጐዳን ፡ እንዳይችል ፡
አምባችን ፡ ያምላክ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

፭ ፤ ግሩም ፡ ጸጋህን ፡ የሰጠኸን ፡
መድኃኒት ፡ ሆይ ፡ ተወደስ ።
ከአንተ ፡ ጋራ ፡ ልጆች ፡ ነን ፡
አ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ።
አምላክን ፡ እናመስግንም ፡

እርሱ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡
ቸር ፡ አባታችን ፡ ሆነ ።

ረስቲን ።

የክርስቶስ ፡ መምጣት ።

ፒሻ

S. T. 142. Am. 102.

፩ ፤ መንገድ ፡ አብጅ ፡ ለጌታ ፡
ጠማማው ፡ ይቅና ።
ይመጣል ፡ ወደ ፡ እኛ ፡
የእስራኤል ፡ ዋና ።
የጽድቅም ፡ ገዥ ፡ ይሆናል ፡
ሥልጣኖቹን ፡ ይጨብጣል ።
ከአብ ፡ የመጣልን ፡
እርሱን ፡ እናመስግን ።

፪ ፤ ነዋሪ ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡
ወደኛ ፡ የመጣ ።

ልብስን ፡ እናንጥፈው ፡
ተፈጸመ ፡ ተስፋ ።
ቃሉ ፡ እውነት ፡ ነውና ፡
ዘምሩ ፡ ሆሣዕና ።
ከአብ ፡ . . . . ።

፫ ፤ ደጅህን ፡ ክፈትለት ፡
ንጉሥህንም ፡ አግባ ።
ሊሰጥ ፡ ለሕዝብ ፡ ደኅንነት ፡
ለዓለሙ ፡ ተስፋ ።
በምድር ፡ ዙሪያ ፡ ሁሉ ፡
እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሊቀኙ ፡
ከአብ ፡ . . . . ።

፬ ፤ የሩሳሌም ፡ ተጣሰ ፡
መቅደሱም ፡ ተፈታ ።
ክህነቱም ፡ ተሻረ ፡
ሉሉ ፡ ዘውዱ ፡ ጠፋ ።
የጌታ ፡ መንግሥት ፡ ገና ፡

በዓለሙ ፡ ሊገዛ ።
ከአብ ፡ . . . . ።

ንብረ ፡ ክርስቶስ ።

፲፯ music Bx. 314

Away in a Manger

S. V. 143. Am. 143.

፩ ፤ ነቢያት ፡ ያዩልን ፡ ቀን ፡
አሁን ፡ ጎሕ ፡ ወጣልን ።
አምላክ ፡ ከወረደልን ፡
በፍቅሩ ፡ ደስ ፡ ይበለን ።
ሆሣዕና ፡ ስግደት ፡ ክብረት ፡
አሁን ፡ እናቅርብለት ።

፪ ፤ ዘውድ ፡ አልተቀዳጀም ፡
እንደርሱ ፡ ግን ፡ የለም ።
ጌጡ ፡ አይታይ ፡ ለዓለም ፡
ሞትን ፡ ግን ፡ ሊያወድም ።
ሆሣዕና ፡ . . . . ።

፫ ፤ ሳለ ፡ ጠቅላይ ፡ ንጉሥ ፡
ሆነ ፡ ትሑት ፡ ዕጉሥ ፡

በርኅራኄ ፡ ነው ፡ ውዱስ ፡
በፍርዱም ፡ ጻድቅ ፡ ቅዱስ ።
ሠላዕና ፡ . . . . ።

፬ ፡ ይህን ፡ ንጉሥ ፡ ጥራ ፡
ወደ ፡ ልብህ ፡ አግባ ።
ካንተ ፡ ኪዳን ፡ ሊጋባ ፡
ቤትህ ፡ ደስታ ፡ ሊመላ ።
ሠላዕና ፡ . . . . ።

O. E.

፲፰

S. T. 145. Am. 103.

ሠላዕና ፡ ለዳዊት ፡ ልጅ ፡
የተባረክ ፡ እርሱ ፡ ነው ። ·
ቡሩክ ፡ ይሁን ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡
የሚመጣ ፡ በአምላክ ፡ ስም ።
ሠላዕና ፡ በአርያም ፡
ሠላዕና ፡ ሠላዕና ።

ቡሩክ ፡ ይሁን ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡
የሚመጣ ፡ በአምላክ ፡ ስም ።
ሖሣዕል ።

፲፱

S. T. 93.

፩ ፡ በጸጋው ፡ እግዚአብሔር ፡
የጠፋውን ፡ ሰው ፡ አዳነ ።
ልጁንም ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡
ላከ ፡ ሊያድነን ።
ዓለም ፡ በኃጢአት ፡ ብዛት ፡
ሰጥሞ ፡ ጠፍቶ ፡ ነበር ።
ጽድቅና ፡ ሕይወት ፡
የአምላክ ፡ ልጅ ፡ በይሞት ፡
ባልተገኘልን ፡ ነበር ።
፪ ፡ ወልድም ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡
ሊፈርድ ፡
አልመጣም ፡ ወደ ፡ እኛ ፡
የፍርድ ፡ መዓት ፡ ግን ፡ እንዲ
በርድ ፡

ተሠዋ ፡ ያለም ፡ ዳኛ ፡
ጠፍቶ ፡ የነበር ፡ ብዕዕናም ፡
ከአብ ፡ በወልድ ፡ ተሰጠን ፡
ተመለሰልን ።
በርሱም ፡ የሚያምን ፡
ይድናል ፡ ለዘላለም ።
፲ ፤ በክርስቶስ ፡ ግን ፡ ያላመነ ፡
አሁን ፡ ተፈረደበት ።
በራሱ ፡ እርሱ ፡ ኰነነ ፡
ጥፋቱም ፡ አይቀርለት ።
የረገጠ ፡ የወልድን ፡ ደም ፡
ብዕዕናን ፡ አያገኝም ።
የአምላክ ፡ በግም ፡
ያስፈርድበታል ፡
ሰማይንም ፡ ይነግል ።
፲፩ ፤ ጌታችን ፡ የሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ሆይ ፡
ነፍስህን ፡ ለወጥህልን ።
በሞት ፡ ጽላ ፡ እንዳንቄይ ፡

በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሞትህልን ።
አ. አምላክ ፡ ጸጋህ ፡ በዝትዋል ።
አ. ያምላክ ፡ ልጅ ፡ ተመስገን ።
በምድር ፡ ሳለን ፡
ምስጋናህ ፡ አንስዋል ፡
በዚያ ፡ ግን ፡ ይደምቃል ።
ረስቲን ።

ፃ

S. T. 153. Am. 100.

፩ ፡ የሩሳሌም ፡ እልል ፡ በዪ ።
የጽዮን ፡ ልጅም ፡ ዘምሪ ።
ንጉሥሽ ፡ ይመጣልና ፡
በምድር ፡ ሁሉ ፡ ሊገዛ ።
፪ ፡ ጸጋና ፡ ጽድቅን ፡ ሊሰጠን ፡
ከአባቱ ፡ ተላከልን ።
ይሰጣልም ፡ ለሰው ፡ ሰላም ፡
ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ በማዳን ።
፫ ፡ ምሥራች ፡ የነገረ ፡ መልአክ ፡
ተልኮልናል ፡ ከአምላክ ።

በርሱ ፡ ያገኘነው ፡ ተስፋ ፡
ይሰጠናል ፡ ታላቅ ፡ ደስታ ።
፱ ፡ ስብሐት ፡ ለአምላክ ፡ በአርያም ፡
በዓለምም ፡ ይሁን ፡ ሰላም ።
ታላቅ ፡ ጸጋ ፡ ላመጣልን ፡
በምሉ ፡ ልብ ፡ እናመስግን ።

N. N.

ልደቱ ፡

፭፩

S. T. 151. Am. 144.

፩ ፡ አ ፡ ግሩም ፡ ጊዜ ፡ አ ፡ ቡሩክ ፡
ሰዓት ።
ለቅዱሳን ፡ ለነቢያት ፡
የታየው ፡ ቀን ፡ መጣልን ።
አሁንም ፡ እንደ ፡ አብ ፡ ሥምረት ፡
የአምላካችን ፡ ምሕረት ፡
ወደኛ ፡ ወረደልን ።
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ሆነልን ።

እናመስግን ፡ በአንድነት ፡
እንወድሰውም ፡ በእምነት ።
፪ ፤ እንዳብም ፡ ፍጹም ፡ አምላክ ፡
ነው ።
እንደኛም ፡ ሆነ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡
ወዳምላክ ፡ ሊያቀርበን ።
የጠፋትን ፡ ይፈልጋል ፤
ሰላሙንም ፡ ይሰጠናል ፤
መድኃኒትም ፡ ሆነልን ።
ጥፉን ፡ ልጁን ፡ እንዲያድን ፡
ያብ ፡ ፈቃድን ፡ ለመፈጸም ፡
ወልድ ፡ ተገለጠ ፡ በዓለም ።
፫ ፤ በመከራችን ፡ አልቅሶ ፡
ሣንቃችንን ፡ አስታውሶ ፡
በመንፈሱ ፡ ሊጠረን ፤
የአብንም ፡ ፈቃድ ፡ ሊገልጥ ፡
ከሣንቅም ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡
ምሉ ፡ ረድኤት ፡ ሊሆነን ።

በሞት ፡ ሕይወት ፡ ሊዋጅልን ፡
የሞት ፡ ጻርን ፡ ታግሦልን ፡
ይከፍትልናል ፡ ሰማይን ።

፪ ፡ ሊያድነኑ ፡ መጥትዋል ፡
የጸጋም ፡ ጀምበር ፡ ወጥትዋል ፡
ኩኖ ፡ የሚይተወነ ።
እርሱን ፡ እንድንከተለው ፡
በእውነት ፡ እረኛችን ፡ ነው ፡
ገንዘቡም ፡ እኛ ፡ ነን ።
በርሱም ፡ ፍጹም ፡ ተስፋ ፡ አለን ፡
እንዲሰጠን ፡ ግሩም ፡ ብዕዕና ።
ለርሱ ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ምስጋና ።

ረዐቲን

ፍ፱

S. T. 151. Am. 144.

፩ ፡ ምስጉን ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ቡሩክ ፡
ሰዓት ፡
ተነበየ ፡ ክነቢያት ፡

ለእኛ ፡ አሁን ፡ መጣ ።
ያ ፡ ታላቅ ፡ ቀን ፡ ያ ፡ ቡሩክ ፡
ሰዓት ፡
የሰማይም ፡ ሰላም ፡ ከዕርቅ ፡
በሰውም ፡ ዘር ፡ ተሰጠ ።
ክቡር ፡ መዝሙር ፡ ይዘምራሉ ፡
ይመጣሉ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ደጆች ።

፪ ፡ በዚህ ፡ አንድ ፡ ልጅ ፡
ተወልዶዋል ፡
አምላክ ፡ ሲሆንም ፡ ለብስዋል ፡
ሥጋችንን ፡ ኸውም ፡ ሆነ ።
ሲመጣ ፡ ጸጋና ፡ ሰላም ፡
ለምድር ፡ ሁሉ ፡ ኃጥአን ፡
ሊሰጥም ፡ ሊረዳቸው ።
ማረ ፡ ራራ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡
ወደ ፡ ምሉ ፡ ጸጋ ፡ ምንጭም ፡
የሚመጡ ፡ ያለ ፡ ጭንቅም ።

፫ ፤ ለመዳናችን ፡ መጥተዋል ፤
ከአባቱ ፡ ተልከዋል ፡
የጸጋ ፡ ፀሓይ ፡ ወጣ ።
ሊጠብቀን ፡ ይወዳል ፤
የእርሱ ፡ ገንዘብ ፡ ሁነናል ፡
እርሱንም ፡ ልንከተል ።
አሁን ፡ ምስጉን ፡ ወደ ፡ እርሱ ፡
የሚደርሱ ፡ በመንግሥቱ ፡
አንድ ፡ ቀን ፡ እርሱንም ፡ ሊመስሉ ።

ሎንዳል ። — B.V.

፳፫

Am. 136. S. T. 90.

፩ ፤ መድኃኒትም ፡ ተገኘ ፡
ከአብ ፡ ተልከዋል ።
ወልድም ፡ እኛን ፡ ሊያድን ፡
ወዳለም ፡ መጥተዋል ።
እርሱ ፡ ብርሃንን ፡ ሰጠ ፡
በጨለማ ፡ ለኖሩ ፡
በመከራና ፡ ሞት ።

፪ ፤ ሰው ፡ ሁኖ ፡ እርሱ ፡ መጣ ፡
የጸጋ ፡ ዘመንም ፡
በምድር ፡ ላይም ፡ ወጣ ፡
ተስፋ ፡ ብርሃን ፡ ሰላም ።
የሞትም ፡ ኃይል ፡ ተሻረ ፡
ከኃጢአትም ፡ ጋራ ።
ሰማይ ፡ ተከፍቶዋል ።

፫ ፤ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ማረን ፡
በእምነት ፡ ልንኖር ፡
ብርሃንህን ፡ ስጠን ፡
በቃልህም ፡ ችሎት ።
ልባችን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡
ይናፍቃል ፡ ክከንቱ ፡
ከዓለም ፡ ዕንቅፋት ።

፬ ፤ ከአባትህ ፡ ተሰጠህ ፡
በሁሉ ፡ ላይ ፡ ሥልጣን ።
አንተም ፡ በደምህ ፡ ዋጀህ ፡
የሕዝብህን ፡ መዳን ።

ሰማይን ፡ ታወርሳለህ ፡
ብዕዕናም ፡ ትሰጣለህ ፡
በመንግሥትህ ፡ ብርሃን ።

፫ ፡ ከአብ ፡ ያገኘኸውንም ፡
ማዳን ፡ ፈቃድህ ፡ ነው ።
የጠፋውን ፡ መንጋህንም ፡
ለሕይወት ፡ መረጥኸው ።
አ ፡ የሱስ ፡ ለኔም ፡ ራራ ፡
እኔንም ፡ ከጌተ ፡ ጋራ ፡
በመንግሥትህ ፡ አኑር ።

ሶንዳል ። ረስቲን ።

ፕሬ

S. T. 156. Am. 130.

Silent night
mus. Ana. 44

፩ ፡ የደስታ ፡ ሌት ፡ የሰላም ፡ ሌት ፡
ጸዳልሽ ፡ ያበራል ።
እረኞች ፡ ብርሃንሽን ፡ አዩ ፡
ወደ ፡ መድኃኒት ፡ ገሰገሱ ።
ሕፃኑን ፡ አገኙ ፡ ሕፃኑን ፡ አገኙ ፡

ፂ ፡ ቅዱስ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ጊዜ ፡
ነቢያት ፡ የነገሩት ።
በዓለም ፡ ጨለማ ፡ ወጣ ፡ ብርሃን ፡
ክብር ፡ ለአምላክ ፡ በሰዎች ፡ መዳን ፡
በምድር ፡ ሁሉ ፡ ሰላም ፡ በምድር ፡
ሁሉ ፡ ሰላም ።

፫ ፡ የደስታ ፡ ሌት ፡ የሰላም ፡ ሌት ፡
የመዳን ፡ ጊዜ ፡ ንጋት ።
ታላቅ ፡ መልካም ፡ የምሥራች ፡ ቀን ፡
ክርስቶስ ፡ ተወልድዋል ፡ በቤተ ፡
ልሔም ፡
የሱስ ፡ የሰላም ፡ ንጉሥ ፡ የሱስ ፡
የሰላም ፡ ንጉሥ ።

ሲግሬድ ።

ፕሯ

S. T. 153. Am. 100.

፩ ፡ ለደስታ ፡ ቀን ፡ ሆነ ፡ ንጋት ፡
ላለም ፡ የምሥራች ፡ ሆነላት ።

መሢሕ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡
ለእረኞች ፡ ተገለጠ ።

፪ ፤ በደንባሮች ፡ በጎች ፡ መሓል ፡
በጎ ፡ እረኛ ፡ ገብቶአል ።
የከዳትንም ፡ ይጠራል ፡
ሰባሮችን ፡ ይጠግናል ።

፫ ፤ ትሑት ፡ ርኅሩኅ ፡ ሁኖ ፡ መጣ ።
እስከ ፡ ሞት ፡ መስቀል ፡ ሊጋዝ ፡
ከሞት ፡ በደሙ ፡ ሊዋጀን ፡
ዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ሊሰጠን ።

፬ ፤ ለጋ ፡ ተክል ፡ የመሰለች ፡
ታላቅ ፡ ዛፍ ፡ ሁና ፡ ጀበበች ።
የማኅበር ፡ ጫፎች ፡ ባለሙ ፡
ለደከሙ ፡ ያጠላሉ ።

፭ ፤ ዝናብ ፡ ምድርን ፡ እንዳራሰት ፡
ቃሉ ፡ ሊሰጥ ፡ ደስታ ፡ ልማት ።
ጽድቅን ፡ ሰላምን ፡ ያመጣል ፡
ፍሬ ፡ ለዘላለም ፡ ያፈራል ።

፮ ፤ ሰማይና ፡ ምድር ፡ ያልፋል ።
የየሱስ ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ይኖራል ።
ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ ሊሰግዱ ፡
አሕዛብ ፡ ስሙን ፡ ሊታመኑ ፡

፯ ፤ በየሱስ ፡ ኃይል ፡ አ ፡ ክርስቲያን ፡
ተነሡና ፡ ሁኑ ፡ ብርሃን ።
የታገለ ፡ ድል ፡ ይነሣል ፡
የታገሠ ፡ ይከብራል ።

፰ ፤ ለቸር ፡ አምላክ ፡ ይሁን ፡
ስብሓት ፡
ስላሳየን ፡ ፍቅር ፡ የውሀት ።
በምሕረቱ ፡ ስላዳነን ፡
እስከ ፡ ዘለዓለም ፡ ይመስገን ።

O. E.
Sweet the Moments
ሽኜ S.S. 316

S. T. 165. Am. 14.

፩ ፤ የማይነገር ፡ ነው ፡
የማይታሰብ ፡ ነው ፡

ታላቅ ፡ ደስታ ፡ የልደት ፡ ቀን ።
እቅርቡ ፡ ክብር ፡ በሁሉ ፡ ምድር ፡
ያምላክን ፡ ፍቅር ፡ እናመስግን ።
፪ ፡ መሢሕ ፡ መጣልን ፡
ሕዝቡን ፡ ሊያድን ፡
ክርስቶስ ፡ ጌታ ፡ ከእሴይ ፡ ሥር ።
ዕርቅን ፡ አመጣ ፡ ተገኘ ፡ ነጻ ፡
ሐሤትን ፡ አድርጊ ፡ ነፍሴ ፡ ሆይ ።
፫ ፡ አምላክ ፡ ይመስገን ፡
ስለሚሰጠን ፡
ጸጋ ፡ ሁሉ ፡ በቸር ፡ ልጁ ።
ወንድም ፡ ሆነልን ፡ ደጅ ፡ ከፈተልን ፡
ልጆች ፡ ሲለን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ።

N. N.

፺፯

S. T. 90. Am. 136.

፩ ፡ እነሆ ፡ ለሕዝብ ፡ ዛሬ ፡
ለደስታ ፡ የሚሆን ፡
የምሥራችን ፡ ወሬ ፡

ልነግር ፡ ለሁሉ ።
መድኅን ፡ በዳዊት ፡ አገር ፡
ተወልድዋል ፡ ድንቅ ፡ ነገር ፡
እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታ ።
፪ ፡ ይህም ፡ ምልክታችሁ ፡
በልብስ ፡ ተጠቅልሎ ፡
ሕፃን ፡ ታገኛላችሁ ፡
በበረት ፡ ተኝቶ ።
እርሱ ፡ ሊነግሥ ፡ አለው ፡
ለምድር ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡
መድኃኒትም ፡ ሊሰጥ ።
፫ ፡ የሰማይ ፡ ጭፍሮች ፡ ብዙ ፡
አብረው ፡ ከመልአኩ ፡
ለአምላክ ፡ ክብር ፡ ሰጡ ፡
እንዲህም ፡ ዘመሩ ፡
ለአምላክ ፡ ክብር ፡ ይሁን ፡
ሰላም ፡ ደግሞ ፡ በምድር ፡
ለሰውም ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ።

ሉንዳል ። — B.V.

፸፰

S. T. 159. Am. 105.

፩ ፡ ጌታ ፡ ከላይ ፡ ተገልጥዋል ፡
በምድር ።
ያምላክ ፡ ልጅ ፡ ተወልድዋል ፡
በቤተ ፡ ልሔም ።
የጥንቱ ፡ ትንቢትም ፡ ተፈጽምዋል ።
የእስራኤል ፡ መሢሕ ፡ መጥትዋል ።

፪ ፡ ጥበቃሽ ፡ ጽዮን ፡ ብዙ ፡
ቈይትዋል ፡
አሁን ፡ ግን ፡ መድኃኒትሽ ፡ ተወ
ልድዋል ፡
ደስታ ፡ በቤትና ፡ ደስታ ፡ በደጆች ፡
ዕርቅና ፡ ሰላም ፡ ለሁሉ ፡ ሰዎች ።

፫ ፡ ከብታቸውን ፡ የሚጠብቁ ፡
እረኞች ፡
ሰሙ ፡ ከአርያም ፡ የመላእክት ፡
ምሥራች ።

ክብር ፡ በላይ ፡ ሰላም ፡ ደግሞ ፡
በምድር ፡
ለሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ የአምላክ ፡
ሥምረት ።

ገብረ ፡ ክርስቶስ ።

፸፱

ልዩ ፡ ዜማ ፡ ፪ ፡

፩ ፡ ሕፃን ፡ ተወልድዋል ፡ በቤተ ፡
ልሔም ፡ ቤተ ፡ ልሔም ።
ደስ ፡ ይበልሽ ፡ የሩሳሌም ።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

፪ ፡ እናቱ ፡ ማርያም ፡ ንጽሕት ፡
ድንግል ፡ ናት ፡ ድንግል ፡ ናት ።
አባቱም ፡ አብ ፡ በሰማያት ።
ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

፫ ፡ በበረት ፡ ውስጥ ፡ ሕፃኑን ፡
አኖሩ ፡ አኖሩ ።
መላእክትም ፡ ለርሱ ፡ ዘመሩ ።

ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

፬ ፡ ሰብአ ፡ ሰገልም ፡ መጥተው ፡
ሠዉለት ፡ ሠዉለት ።
ወርቅና ፡ ዕጣን ፡ ከርቤም ፡ ሰጡት ።
ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

፭ ፡ መድኃኒት ፡ ያ ፡ ሕፃን ፡ ሁኖልናል ፡
ሁንዋል ፡ ጭንቃችንም ፡
ተሸርዋል ።
ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

፮ ፡ የአምላክ ፡ ልጅ ፡ በፍቅሩ ፡
መጣልን ፡ መጣልን ።
በእርሱም ፡ ደስ ፡ ይበለን ።
ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

፯ ፡ አወረደልን ፡ ከአብ ፡ ሥምረቱን ፡
ሥምረቱን ።
በደስታ ፡ እናያለን ፡ ፊቱን ።
ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

፰ ፡ መላእክት ፡ ስለርሱ ፡ እንደ
ዘመሩ ፡ ዘመሩ ፡

እናንተም ፡ ምስጋናውን ፡ አውሩ ፡
ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

፱ ፡ ለቸሩ ፡ አምላክ ፡ ይሁን ፡
ክብር ፡ ክብር ፡
ሰላምም ፡ በኛ ፡ በምድር ።
ሃሴ ፡ ሉያ ፡ ሃሴ ፡ ሉያ ።

ገፀረ ፡ ክርስቶስ ፡

፴

ልዩ ፡ ዜማ ፡ ፫ ፡

፩ ፡ ሕፃን ፡ ተወለደ ፡ በዚህ ፡ ሌት ።
ያን ፡ ቅዱስ ፡ ሕፃኑን ፡ እናክብር ።
በእርሱ ፡ ላይ ፡ አለ ፡ የአብ ፡
ሥምረት ፡
በእኛም ፡ ትምህርቱ ፡ ይዳብር ።
ይኸ ፡ ሕፃን ፡ ባይወለድም ፡
በጠፋነ ፡ ሁላችንም ፡
አውን ፡ ግን ፡ ሕይወት ፡ አለን ።
አ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመስገን ።

በአንተ ፡ ተስፋ ፡ አግኝተን ፡
ላንተ ፡ እንሰግዳለን ።

፪ ፡ እረኞች ፡ መንጋቸውን ፡
ሲጠብቁ ፡
በሌሊት ፡ በሜዳ ፡ ሲቄዩ ፡
በሰሙት ፡ ነገር ፡ ተደነቁ ፡
የአምላክን ፡ ክብርም ፡ አዩ ።
መልአክ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ዘመረ ፡
መድኅን ፡ ዛሬ ፡ ተወለደ ፤
እርሱም ፡ በዳዊት ፡ አገር ፡
ጌታችን ፡ ነው ፡ በርሱም ፡ ሥልጣን ፡
የአምላክ ፡ የግርማው ፡ ብርሃን ፡
ተገለጠ ፡ በምድር ።

፫ ፤ መላእክትም ፡ ደግሞ ፡
በታላቅ ፡ ቃል ፡
አምላክን ፡ ይወድሱ ፡ ጀመር ፡
በቅዱሳን ፡ በሰማይ ፡ ጸዳል ፡
ለዘላለም ፡ እንደሚዘመር ፡

ለአምላክ ፡ ውዳሴ ፡ ይሁን ፡
በምድርም ፡ ሰላም ፡ ይሁን ፡
በጎም ፡ ፈቃድ ፡ አይተወን ።
አ ፡ ርኅሩኅ ፡ አምላክ ፡ ተመስገን ፡
ከልጅህ ፡ ጋር ፡ ከሰጠኸን ፡
ከጸጋህ ፡ አትለየን ።

ረዘቲኑ ።
Gentle Jesus
S. S. 149

ሽሸ
S. T. 57. Am. 183.

፩ ፡ ያብ ፡ ሥምረት ፡ ተገለጠች ፡
ንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ወለደች ።
ያምላክ ፡ ልጅ ፡ ተወልዶዋል ፡
በዕጹብ ፡ ያስደንቃል ።

፪ ፡ ግሩም ፡ ተአምራት ፡ አይተናል ፡
ባምላክ ፡ መንፈስ ፡ ሁንዋል ።
የዘላለም ፡ ያምላክ ፡ ቃል ፡
እንደ ፡ ሰው ፡ ተወልዶዋል ።

፫ ፤ ሳይደርስበት ፡ ኃጢአት ፡
የሰውን ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡
የሚሸር ፡ ተወለደ ፡
ከሥጋም ፡ ተዋሐደ ።

፬ ፤ ፍጹም ፡ አምላክ ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡
በመሆኑ ፡ መድኅን ፡ ነው ።
በሥቃይና ፡ ሕማም ፡
አግኝቶልናል ፡ ሰላም ።

፭ ፤ ጥንት ፡ ከአብም ፡ ወጥተዋል ፡
ወደ ፡ አብም ፡ ዓርግዋል ።
በቀኙም ፡ ተቀምጥዋል ፡
ሁሉም ፡ ይገዛለታል ።

፮ ፤ ሞትን ፡ በምላኪ ፡ ኃይል ፡
ለዘላለም ፡ ሽርዋል ።
ድል ፡ በብርቱ ፡ ውጊያ ፡
ነሥትዋል ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።

፯ ፤ አምላክን ፡ በአርያም ፡
እናመስግን ፡ በሰላም ።

እኛን ፡ መንፈሱም ፡ ይምራ ፡
ምድሪቱም ፡ ጽድቅ ፡ ታፍራ ።

ረስቲን ።

፴፪

S. T. 106.

፩ ፤ ሕፃን ፡ ተወልዶልናል ፡
ልጅም ፡ ተሰጠን ፡
ከአምላክ ፡ በደም ፡
በሥጋም ፡ ተገናኘን ።
ከሰው ፡ ዘር ፡ ከሴቶቹ ፡ እናቱን ፡ መርጠ ፡
በውርደት ፡ ተወለደ ፡ ፍቅሩን ፡ ገልጦ ።

፪ ፤ ፈጣሪ ፡ ከፍጥረቱ ፡
ጋራ ፡ ተዛምዶ ፡
ከኃጢአተኞችም ፡ ቅዱስ ፡ ተጣምዶ ፡
አብ ፡ ወልድን ፡ ከላከ ፡
ሊሆን ፡ ዘመዳችን ፡
ምሕረቱን ፡ ላሳየን ፡
ይረግ ፡ ምስጋናችን ።

፫ ፤ በውድቀቱ ፡ አዳም ፡
ላወረሰን ፡ ሁሉ ፡
መድኃኒት ፡ ተገኘ ፡ በበረት ፡ በጎሉ ።
ስርየት ፡ ልናገኝ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችን ፡
የዓለም ፡ ፈራጅ ፡ ሁንዋል ፡
ወንድማችን ።

፬ ፤ የታሠሩን ፡ ሁሉ ፡
አወጣ ፡ አርነት ፡
ከሞት ፡ ከቅጣትም ፡ አበጀ ፡ ነጻነት ።
ጠላቶቹን ፡ ሁሉ ፡ በኃይል ፡ ድል ፡
ይነሣል ።
ለኃጢአተኞች ፡ ይቅርታን ፡
ይለግሳል ።

፭ ፤ በበረት ፡ በጎሉ ፡ የተኛ ፡ ሕፃኑ ፡
ሰው ፡ እርሱን ፡ ሊወድስ ፡
አይበቃውም ፡ ልሳኑ ።
በውርደቱ ፡ ክብሩ ፡ ተደብቆ ፡
ባይታይም ፡

መናንን ፡ ብዕዕናን ፡ ግን ፡ ዋጀ ፡
ለዓለም ።

፮ ፤ ይህንን ፡ ብዕዕናም ፡ በቃሉ ፡
ይሰጣል ፡
በቃሉም ፡ የጸጋ ፡ ፈቃዱን ፡ ይገልጣል ።
ስጦታውንም ፡ ለግሶ ፡ ለሁሉ ፡
ሲሰጠው ፡
ልባችንን ፡ አጽንቶን ፡ ቸል ፡
አንበለው ።

፯ ፤ ይልቅ ፡ ልንቀበለው ፡
እንስገድለት ፡
እንዲህም ፡ ስንል ፡ እንዘምር ፡
በእምነት ።
ብምድር ፡ ተወልደህ ፡ መዳን ፡
የሆንህልን ፡
አ ፡ ቸር ፡ ወንድማችን ፡
አ ፡ አምላክ ፡ ተመስገን ።

ፀፐ

S. T. 161. Am. 115.

፩ ፡ የልደት ፡ ቀን ፡ ሲመጣ ፡
የቤተ ፡ ልሔም ፡ ሕፃን ፡
በበረት ፡ ላይ ፡ የተኛ ፡
ይሰጠናል ፡ ብርሃን ።

፪ ፡ በመውረድህ ፡ ወደኛ ፡
ፍቅርህ ፡ ተገለጠ ።
በኃጢአት ፡ ዘመናችንን ፡
እንዳናሳልፈው ።

፫ ፡ የሰው ፡ ያስፈልገኛል ፡
የሕፃናት ፡ ወዳጅ ፡
በእኔ ፡ እንዳታዝን ፡
ልከተልህ ፡ እርዳኝ ።

N. N.

ፀፀ

Am. 120.

፩ ፡ ኑ ፡ አክብሩት ፡ ጌታን ፡
ስገዱለት ፡

የልባችሁንም ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉለት ፡
ኑ ፡ አምልኩት ፡ ስብሓትንም ፡
አቅርቡለት ።

ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ኑ ፡
እርሱን ፡ ልትወድሱ ፡
ወደርሱም ፡ ቅረቡ ፡
እርሱን ፡ ልታከብሩ ።

፪ ፡ አምላክ ፡ መጥትዋል ፡
በበረት ፡ ተወልድዋል ፡
የአብ ፡ ልጅ ፡ ለዓለም ፡ ተገልጸለታል ።
ክብር ፡ ለአብ ፡ ስብሓትም ፡ ይገባል ።

ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ኑ ፡ . .

፫ ፡ አምን ፡ ጌታችን ፡ ሆይ ፡
በፊታችን ፡ ወድቀን ፡
እንሰግድልህ ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ።
ለኛ ፡ ስትል ፡ ከዙፋንህ ፡ ወርደሃል ።

ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ ኑ ፡ . .

From Greenland's Icy Mts. S. S. 1070

፴፩

S. T. 90. Am. 136.

፩ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ በረት ፡
ግሩም ፡ ነገር ፡ አይተናል ።
የአምላካችን ፡ ምሕረት ፡
አውን ፡ ገሀነኖናል ።
በዳዊት ፡ አገር ፡ መድኅን ፡
ዛሬ ፡ ተወለደልን ፡
እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታ ።
፪ ፡ በበረት ፡ ውስጥ ፡ የተኛ ፡
ሕፃን ፡ ጌታችን ፡ ነው ።
ተወለደ ፡ እንደኛ ፡
እንዳብ ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ነው ።
ለእርሱም ፡ ይሰግዳሉ ፡
የምድር ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ።
መድኃኒታችን ፡ ነው ።
፫ ፡ እኛም ፡ እንደ ፡ መልአኩ ፡
አውን ፡ እናመስግን ።

አንድ ፡ ልጁን ፡ በመላኩ ፡
አምላክ ፡ ሁሉን ፡ ሰጠን ፡
ለአምላካችን ፡ ክብር ፡
ሰላም ፡ በዚህ ፡ በምድር ፡
ለሰውም ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ።

ረስቲን ።

፴፪

S. T. 150.

፩ ፡ የልደት ፡ ማታ ፡ እንዴት ፡
ያበራል ፡
መብራት ፡ ሲለኰስ ፡ በልብ ፡ በቤትም ።
የመላእክት ፡ መዝሙር ፡ አውን ፡
ይሰማል ፡
ከጥንቱ ፡ ጀምሮ ፡ ይደመላል ።
ለአምላክ ፡ ይሁን ፡ ምስጋና ፡
በምድርም ፡ ሰላም ፡
ለሰው ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ ሲሉ ፡
ዘመሩ ።

የልደት ፡ ማታ ፡ እንዴት ፡ ያበራል ፡
መብራት ፡ ሲለኰስ ፡ በልብ ፡ በቤትም ።

፪ ፡ አምላክ ፡ ለምድር ፡
የሰጠው ፡ ስጦታ ፡
ለኃጢአተኞች ፡ መዳን ፡ ይሆናል ።
ፀሓይ ፡ በዓለም ፡ እንደሚወጣ ፡
ጨለማን ፡ የሱስ ፡ አሸንፍዋል ።
ሕዝብ ፡ በጨለማ ፡ የሔዱ ፡ በሞት ፡
አገርም ፡ በጽላም ፡ የኖረ ፡ ሕዝብ ፡
ታላቅ ፡ ብርሃን ፡ አየ ።
አምላክ ፡ ለምድር ፡ የሰጠው ፡ ስጦታ ፡
ለኃጢአተኞች ፡ መዳን ፡ ይሆናል ።

፫ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡
የተሰጠ ፡
ዕርቅና ፡ ጽድቅ ፡ ሕይወትና ፡ ሰላም ።
መድኃኒታችን ፡ የወይን ፡ ዛፍ ፡ ሆነ ፡
የሕይወት ፡ ፍሬ ፡ ከርሱ ፡ አገኘን ።
አንድ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ተሰጠን ፡

ሕፃን ፡ ተወልድዋል ።
አለቅነቱም ፡ በጫንቃው ፡ ላይ ፡
ይሆናል ።
በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ የተሰጠ ፡
ዕርቅና ፡ ጽድቅ ፡ ሕይወትና ፡ ሰላም ።

ተአ ።

፬

ልዩ ፡ ዜማ ፡ ፩ ።

ስብሓት ፡ ስብሓት ፡ ስብሓት ፡
ለአምላክ ፡ በአርያም ፡
ሰላምም ፡ በምድር ።

ለሰዎችም ፡ የአምላክ ፡
ሥምረት ፡ ይሁን ።

ለሰዎችም ፡ የአምላክ ፡ ሥም
ረት ፡ ይሁን ።
ስብሓት ፡ ለአምላክ ፡ በአርያም ፡
ስብሓት ፡ ለአምላክ ፡ በአርያም ፡
ሰላምም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡
ሰላምም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡

ለሰዎችም ፡ የአምላክ ፡ ሥም
ረት ፡ ይሁን ፡ ስብሓት ፡ . . .
አ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ እኔን ፡
አበርታ ፡ እምነቱን ።
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በልቤ ፡
ንጉሥ ፡ ሆኖ ፡ ይግዛ ።
ሰላሙን ፡ ያሳድርብኝ ፡
ብርሃኑን ፡ ያብራልኝ ፡
መድሓን ፡ ተወለደልኝ ፡
በርሱም ፡ ሰላም ፡ አለኝ ።

ሀብተ ፡ አብ ፡ ወ. ማ.

ሕማማቱ ።

ፀጀ

S. T. 192. Am. 159.

፩ ፡ የሱስ ፡ ለዓለም ፡ ሲል ፡
መ·ትዋል ።
አምላክ ፡ ስጠኝ ፡ ቅዱስ ፡ ማስተዋል ።

እንድድንበት ፡ ከሱኔ ፡
እርሱ ፡ በመስቀል ፡ ሞተ ፡ ለኔ ።
፪ ፡ እንዴት፡ ይገርማል ፡ ታላቅ፡
ፍቅሩ ።
ማንም ፡ አይወደኝ ፡ እንደ ፡ እርሱ ፡
እርሱ ፡ ከዳነኝ ፡ በመሞቱ ፡
ሕይወቱን ፡ ልስጠው ፡ ለክብረቱ ።
፫ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ልጅህ ፡
አድርገኝ ።
ከሰይጣን ፡ ወጽመድ ፡ ሁሉ ፡ ፍታኝ ።
አንተን ፡ ልከተል ፡ አስተምረኝ ፡
ላንተም ፡ ልሆን ፡ በፍቅርህ ፡ እርዳኝ ።

ረስቲን ።

ፀፀፀ

S. T. 185.

፩ ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡ ጤና ፡ ሰላምም ፡
ልትሰጠኝ ፡ መ·ተሃል ።
በማይነገረው ፡ ሕማምም ፡

ነፍሴን ፡ ከሞት ፡ ገዝተሃል ።
ከጥፋት ፡ አውን ፡ ድኛለሁ ፡
ሕይወትንም ፡ እወርሰለሁ ።
ይሁንልህ ፡ ውዳሴ ፡
ጌታ ፡ የሱስ ፡ አምላኬ ።

፪ ፤ ስለ ፡ መረረ ፡ ሕማምህ ፡
ልቤ ፡ ያመሰግናል ።
በሥቃይህ ፡ በድካምህ ፡
ሕይወት ፡ ተገኝቶልኛል ።
ልትሰርይ ፡ የኔን ፡ በደል ፡
ሞትን ፡ ቀምሰሃል ፡ በመስቀል ።
ይሁንልህ ፡ ውዳሴ ፡
ጌታ ፡ የሱስ ፡ አምላኬ ።

ረስቲን ።

Remember Me
S. S. 630
Une. 93

ማ

S. T. 181. Am. 148.

፩ ፤ አልረሳውም ፡ ያንን ፡ ጊዜ ፡
በጌቴሴማኒ ።

በጣርህ ፡ ደም ፡ ሲያልብህ ፡
ስለኔ ፡ አምላኬ ።
አልረሳውም ፡ አልረሳውም ፡
ከቶ ፡ አልረሳውም ፡
የብርቱ ፡ ጣርህን ፡ ጊዜ ፡
በጌቴሴማኒ ።

፪ ፤ በዚያ ፡ ስፍራ ፡ ባታክልቱ ፡
በልቤ ፡ አየሁህ ።
ቤዛ ፡ ሁነህ ፡ የፍርድ ፡ መዓት ፡
እንደ ፡ ተቀበልህ ።
አልረሳውም ፡ አልረሳውም ፡ . . ።

፫ ፤ ወዳጆችህ ፡ ሁሉ ፡ ክዱህ ፡
አልራራልህም ፡ አብ ።
ያ ፡ ብርቱ ፡ ችግርህ ፡ ጊዜ ፡
አይመዘንም ፡ በሰብ ።
አልረሳውም ፡ አልረሳውም ፡ . . ።

፬ ፤ ፍቅሬ ፡ ቢበርድብኝ ፡ ላንተ ፡
ክቡር ፡ መድኃኒቴ ፡

ሕማማትህን ፡ አሳስበኝ ፡
አሳየኝ ፡ ቍስልህን ።
እንዳልረሳው ፡ እንዳልረሳው ፡
ይህን ፡ እንዳልረሳው ፡
የብርቱ ፡ ጣርህን ፡ ጊዜ ፡
በጌቴሴማኒ ።
፮ ፡ ስለኔ ፡ ነው ፡ ስለኔ ፡ ነው ፡
ደምህ ፡ የፈሰሰ ።
እንዳመሰግንህ ፡ ጌታ ፡
ክፈትልኝ ፡ አፌን ።
እንዳልረሳው ፡ እንዳልረሳው ፡ . . ።

ሲግሬድ ።

ማ፩

S. T. 49. Am. 139.

፩ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ እኛ ፡
መከራ ፡ ተቀበለ ።
እርሱም ፡ እንደ ፡ በደለኛ ፡
በንጪት ፡ ላይ ፡ ተሰቀለ ።

ቤዛ ፡ እርሱ ፡ ሠውንዋል ፡
በኛም ፡ ፈንታ ፡ መ·ትዋል ።
፪ ፡ በሕማማቱ ፡ በሞቱም ፡
ምሕረት ፡ ተዋጅ·ቶልናል ።
በትንሣኤውም ፡ በሕይወቱም ፡
ጽድቅም ፡ ተገኝ·ቶልናል ።
በዕርገቱም ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ስፍራ ፡ ሰጠን ፡ በሰማይ ።
፫ ፡ ምስጉን ፡እርሱን ፡የሚያምን ፡
የሚቀበል ፡ ጸጋውን ።
የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ፡
ችጋረኛ ፡ ቢሆንም ።
ከምድር ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡
ይገባል ፡ በሃይማኖት ፡

ረስቲን ፡ ሉንዳል ።

ማ፪

S. T. 186. Am. 67.

፩ ፡ የሱስ ፡ሆይ ፡ያንተ ፡ሕማማት ፡
ያንተ ፡ ቍስልና ፡ ሞት ፡

ይሰጠኛል ፡ መጸናናት ፡
በሚደርስብኝ ፡ ጭንቀት ።
ሥጋዬ ፡ ቢፈትነኝ ፡
ሕማምህን ፡ አሳስበኝ ።
ጉዳት ፡ እንዳይወርድብኝ ፡
ሥጋዊ ፡ ምኞትን ፡ አጥቃልኝ ።

፪ ፡ ክፉ ፡ ሥጋ ፡ ወደ ፡ ፍትወት ፡
ቢያስመኝኝ ፡ ለውድቀት ፡
ቀኑስልህን ፡ ግን ፡ ስመለከት ፡
ሊሆነኝ ፡ አዲስ ፡ ድፍረት ።
ሰይጣንም ፡ ቢረትነኝ ፡
የጸጋህን ፡ ኃይል ፡ ሳገኝ ፡
በቶሎ ፡ እስኪሸሽልኝ ፡
ለማሸነፍ ፡ ልታበቃኝ ።

፫ ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡ የልቤ ፡ ጌታ ፡
በውስጤ ፡ ከኖርህልኝ ፡
ጭንቅ ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ቢበዛ ፡
ከሰላምህ ፡ አይለየኝ ።

ዋጀኸኝ ፡ ለአንተ ፡ ኑኝ ፡
ምን ፡ አለ ፡ የጐደለኝ ።
ሁሉ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ሳለኝ ፡
ብዕዕናን ፡ አታስቀርብኝ ።

ሉንዳል ።

፵፫

S. T. 183.

፩ ፡ የመስቀል ፡ ውርደት ፡ ስደብም ፡
ተሸከምህልን ፡ ጌታ ።
የጠፉትን ፡ ለማዳንም ፡
ሞትህልን ፡ በጎልጎታ ።
አ ፡ ፍቅር ፡ ግሩም ፡
አ ፡ ቅዱስ ፡ ደም ።
ስለኛ ፡ የተሰጠ ።

፪ ፡ የመስቀል ፡ ሽክም ፡ ከባድ ፡ ነው ፡
የኛ ፡ ዕዳ ፡ ሲጨመር ።
ምስጋና ፡ ከማይሰጥህ ፡ ሰው ፡
እኛ ፡ እንዳንደመር ።

አስታውሰን ፡
ሙቅ ፡ ፍቅርህን ፡
ልባችንን ፡ የሚሰብር ።

ፒ ፡ የመስቀል ፡ መንገድ ፡ መረጥህ ፡
ትተህ ፡ ያባትህ ፡ ግርማ ።
ልታስረዳን ፡ ታላቅ ፡ ፍቅርህ ፡
ተዋረድህ ፡ ስለኛ ።
ይታገሣል ፡
ያሸንፋል ፤
አ ፡ ጌታ ፡ ያንተ ፡ ፍቅር ።

ፀ ፡ በመስቀልህ ፡ ሥታይ ፡ ጌታ ፡
ሞትን ፡ ያስወገድህልን ።
እኛ ፡ ድል ፡ ነሥተን ፡ በደስታ ፡
ቤትህን ፡ መግቢት ፡ አስችለን ።
ባንተ ፡ እምነት ፡
ለነፍስ ፡ ዕረፍት ፡
አሁን ፡ በጸማህ ፡ አለን ።

N. N.

ማፀ

S. T. 187.

ፅ ፡ ኑ ፡ ሁላችን ፡ እንመልከት ፡
የጌታችንን ፡ ሥቃይ ።
ኃጢአትን ፡ ሲያስወግድ ፡
መከራውን ፡ እንወያይ ።
የጌታችንን ፡ ሕመም ፡
የሚመስል ፡ አልነበረም ።

ቊ ፡ ቅዱስ ፡ አካሉን ፡ ችንካሩ ፡
ገትሮ ፡ አቁሰለ ።
የሸህ ፡ ዘውድ ፡ ነው ፡ በግምባሩ ፡
መቅሠፍትም ፡ ተቀበለ ።
የጌታችንን ፡ ሕመም ፡
የሚመስል ፡ አልነበረም ።

ቮ ፡ በመጨረሻም ፡ በመስቀል ፡
እጅግ ፡ ከተጣቀየ ፡
አሁን ፡ መንፈሱን ፡ ተቀበል ፡
ሲል ፡ ላባቱ ፡ ጸለየ ።

የጌታችንን ፡ ሕመም ፡
የሚመስል ፡ አልነበረም ።

፪ ፡ ያምላክ፡መቅደስ፡መንጦላዕት፡
ያን ፡ ጊዜ ፡ ተቀደደ ።
የማስታረቅም ፡ መሥዋዕት ፡
ፈጽሞ ፡ ተጨረሰ ።
የጌታችንን ፡ ሕመም ፡
የሚመስል ፡ አልነበረም ።

፫ ፡ ሰው፡ሆይ፡ስለ፡ኃጢአትህ፡
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሙትዋል ።
እስከ ፡ መስቀል ፡ ሞት ፡ ጥፋትህ ፡
መድኅኑን ፡ አድርስዋል ።
የየሱስን ፡ ፍቅርም ፡
የሚመስል ፡ አልነበረም ።

ረዳቲን

ማሬ

S. T. 189 Am. 162

፩ ፡ አ ፡ ያምላክ ፡ በግ ፡ ስለኛ ፡

በመስቀል ፡ ላይ ፡ ተሠዋህ ።
አ ፡ አንተ ፡ ትዕግሥተኛ ፡
አ ፡ አንተ ፡ ርኅሩኅ ፡ የዋህ ፡
ፍርዳችንን ፡ ተሸከምኸው ፡
የሞትን ፡ ኃይል ፡ አሸነፍኸው ።
ሰላም ፡ ስጠን ፡ አ ፡ የሱስ ።

ረዳቲን ።

When I Survey the
ማሬ Wondrous Cross
mus. dna. 423
Am. 186

፩ ፡ስመለከት፡ያን፡ድንቅ፡መስቀል፡
መድኅኔ ፡ የሞተበትን ፡
እንቀዋለሁ ፡ ሕይወቴን ፡
ትምክሕቴም ፡ ከንቱ ፡ ይሆናል ።

፪ ፡ በቅዱስ ፡ መስቀልህ ፡ በቀር ፡
እንዳልመካ ፡ ከልክል ፡ ጌታ ።
ሥጋዬን ፡ ጥዬ ፡ በአንተ ፡ እግር ፡
እሰግዳለሁ ፡ ጸጎልጎታ ።

ቮ ፡ እይ ፡ ከራሱ ፡ ከእጁ ፡ ከእግሩም ፡
የከበረ ፡ ደሙ ፡ ፈስዋል ።
እንዴት ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ ሁንዋል ፡
የሚሸከም ፡ የኔን ፡ መርገም ።

ፀ ፡ ዓለምን ፡ ምሉ ፡ ብሰጥህ ፡
ያንስብህ ፡ ነበር ፡ ስጦታው ።
ነፍሴንና ፡ ሕይወቴን ፡ ይኸው ፡
ተቀበለኝ ፡ ሳቀርብልህ ።

ሻሺ

S. T. 112 Am. 179

ፅ ፡ ያፈሰስህልን ፡ ደምህን ፡
አ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመስገን ።
ከሰይጣን ፡ ተንኰልና ፡ ኃይል ፡
በሞትህ ፡ አድነኸናል ።

ፁ፡አ፡ፍጹም፡አምላክ፡ፍጹም፡ሰው፡
ና ፡ ጸሎታችንን ፡ ስማው ።

የታሰርነበት ፡ ወጽመዳን ፡
በኃይልህ ፡ በጥሰው ፡ አውን ።
ፂ ፡ ከኃጢአትም ፡ ጠብቀን ፡
መስቀል ፡ ሲከብድም ፡ ደግፈን ፡
ጭንቅም ፡ እንዳያሸንፈን ፡
ቅዱስ ፡ ረድኤትህን ፡ ስጠን ።

ፃ ፡ አ ፡ የሱስ ፡ ወንድማችን ፡ ነህ ፡
በሁሉም ፡ ረድኤታችን ፡ ነህ ።
ከመከራችን ፡ አድነን ፡
ካንተም ፡ ዘንድ ፡ ሕይወትን ፡ ስጠን ።

ረስቲን ።

Jesus Keep Me Near the Cross
ሚ. Hymn. 62

Am. 6 S. T. 493

ፄ ፡ የሱስ ፡ በመስቀል ፡ ሳለ ፡ ከዚያ ፡
የክብር ፡ ምንጭ ፡
ለሁሉ ፡ ነጻ ፡ ሰጭ ፡ በቀራንዮ ፡ ተራራ ።
መስቀልህ ፡ መስቀልህ ፡ ለዘላለም ፡
ይሁን ፡

ነፍሴ ፡ ዕረፍት ፡ ስታገኝ ፡ በሰማይ ፡
ታርፋለች ።
ፙ ፤ ከመስቀልህ ፡ አጠገብ ፡ ነፍሴ ፡
ስትጨነቅ ፡
የጥኋት ፡ከዋክብት ፡በዙሪያዩ ፡ አበሩ ።
መስቀልህ ፡ . . . . . .
ፚ ፤ መስቀልህ ፡ የእግዜር ፡ በግ ፡
ሰላምህ ፡ በፊቱ ፡
ከቀን ፡ ወደ ፡ ቀን ፡ እርዳኝ ፡ ና ፡
ወደኔ ፡ ቶሎ ።
መስቀልህ ፡ . . . . . .
ፚ ፤ ከመስቀሉ ፡ አጠገብ ፡
እጠብቃለሁ ፤
ተስፋና ፡ መታመንህ ፡ ለዘላለም ፡
ይሁን ።
መስቀልህ ፡ . . . . . .

ፚፙ

Am. 8.

ፚ ፤ አዳኜ ፡ ደሙ ፡ ፈሰሰ ፡

ንጉሤ ፡ ሞተልኝ ፤
ራሱ ፡ ለውርደት ፡ ደረሰ ፡
እኔን ፡ ሊያድነኝ ።
በመስቀል ፡ በመስቀል ፡ ብርሃን ፡
በየሁበት ፡
የልቤ ፡ ሸክም ፡ በቀለለበት ፡
በእምነት ፡ነው ፡ማየትን ፡ያገኘሁ ፡
በዚህ ፡ ደስታዬን ፡ አሳያለሁ ።
ፙ ፤ ስላደረግሁት ፡ በደል ፡ ነው ፡
በዛፍ ፡ ላይ ፡ ጭንቅቱ ፤
ርኅሩኅ ፡ ነው ፡ ሰጪ ፡ ጸጋውን ፡
ለዚህ ፡ ነው ፡ መሞቱ ።
በመስቀል ፡

ፚፚ

S. T. 189. Am.162

ፚ ፤ ካምላክ ፡የራቅነውን ፡ኃጥኣን ፡
ልጆቹ ፡ እንዲያደርግ ፡
በንጹሕ ፡ ደሙ ፡ ገዛን ፡

ያ ፡ ቅዱስ ፡ የአምላክ ፡ በግ ።
በልብህ ፡ ሥቃያችንን ፡
ተሸክመህ ፡ ልባችንን ፡
አዳንክ ፡ አ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ።

፪ ፡ ብርቱ ፡ የሚያስደንቅ ፡
ሥቃይ ፡ ሲያስፈራራህ ፡
መንፈስህም ፡ ሲጨነቅ ፡
በጻርህ ፡ ለኛ ፡ ራራህ ።
ቁንቃችንን ፡ ብታስብም ፡
ሕማሙን ፡ አልተሰቀቅህም ።
ተመስገን ፡ ጌታ ፡ የሱስ ።

፫ ፡ እኛ ፡ እንድንባረክ ፡
ተጫነ ፡ በንተ ፡ መርገም ።
ጻርህ ፡ እንዲት ፡ ይተረክ ፡
መስቀሉን ፡ ስትሸከም ፡
የመቅሠፍት ፡ ጽዋ ፡ ጠጥተህ ፡
ስለኛ ፡ ነፍስህን ፡ ሰጥተህ ፡
አዳንኸን ፡ ጌታ ፡ የሱስ ።

፬ ፡ የሱራፊልን ፡ ቁጥሮች ፡
ሁሉ ፡ መጥራት ፡ ሲቻልህ ፡
የአርያምም ፡ ኃይሎች ፡
ሲታዘዙ ፡ ለኃልህ ፡
በምድራችን ፡ ታስረህ ፡
እሞት ፡ ድረስም ፡ ታዝዘህ ፡
ሞትህልን ፡ ጌታ ፡ የሱስ ።

፭ ፡ ግን ፡ ምሕረት ፡ ያላሳየህ ፡
አምላክ ፡ ለእኔ ፡ ራራ ።
ልቤም ፡ ስለ ፡ ሥቃይህ ፡
ይሆናል ፡ ካንተ ፡ ጋራ ።
ልቤን ፡ እሰጥሃለሁኝ ፡
ለአንተም ፡ እሆናለሁኝ ፡
ለአንተ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ።

ረስተን ።

Ah, Happy Day
S.S. 866 #

፶፩

S. T. 588, 369

፩ ፡ ፍርዳችንን ፡ የወሰድኸው ፡
መስቀልን ፡ የተሸከምኸው ፡

ከሞትም ፡ ኃይል ፡ ያወጣኸን ፤
አ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አድምጸን ።
አ ፡ የሞትህልን ፡ አድነን ።
ስማልን ፡ ጸሎታችንን ።

፪ ፡ ታላቅ ፡ ሥራህ ፡ ተፈጸመ ፡
ፍርድ ፡ ምሕረቱን ፡ አተመ ።
የፍርድ ፡ አምላክ ፡ ለኃጢአት ፡
ከሰጠ ፡ በቂውን ፡ ቅጣት ፡
መሐሪ ፡ አምላክ ፡ ልጆቹ ፡
አደረገን ፡ በምሕረቱ ።

፫ ፡ ግን ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡ ካልረዳኸን ፡
እንዴት ፡ ደካሞች ፡ እኛ ፡ ነን ።
ልጅነታችን ፡ በቀላል ፡
ከእኛ ፡ ይጠፋብናል ።
ያምላክ ፡ ልጆች ፡ ያደረግኸን ፡
አ ፡ የሱስ ፡ አንተ ፡ ጠብቀን ።

፬ ፡ አትራቅብን ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡
ሁለገዜ ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ቄይ ።

በፈተና ፡ አበርትተህ ፡
በትግልም ፡ አጠንክረህ ፡
በሕይወቱም ፡ በሞቱም ፡ ጻር ፡
በደምህ ፡ ኃይል ፡ ሁን ፡ ከኛ ፡ ጋር ።

ረስቲን ።

፶፪

S. T. 451.

፩ ፤ ከአምላክ ፡ ፍርድ ፡ ልታድነን ፡
በመስቀል ፡ ሞት ፡ የገዛኸን ፡
አ ፡ መድኅኔ ፡ አ ፡ አምላክ ፡
መርገሜን ፡ የሚደመስስ ፡
ደምህ ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ ይፍሰስ ፤
እኔን ፡ ርጉም ፡ ይባርክ ።
ያ ፡ ቅዱስ ፡ ደምም ፡ ኃይል ፡ ይስጠኝ ፡
ከፈተናም ፡ ይጠብቀኝ ፡
በእንብ ፡ ዱሐም ፡ ስሔድ ፡ ይምራኝ ፤
በሞት ፡ በሕይወትም ፡ ይርዳኝ ።
ጕዞዬንም ፡ ከጨረስሁ ፡ ከደረስሁ ፡

በፍቁር ፡ ዕቅፍህ ፡ ውስጥ ፡ ያግባኝ ።

ረዳቲን ።

ሃቮ

S. T. 35. Am.154.

፩ ፡ የሱስ ፡ በመስቀል ፡ ሞተልን ።
እንማጠን ፡ በፍቅሩ ።
አምላክ ፡ ሁሉ ፡ ዓመፃችን ፡
ተወልን ፡ ስለ ፡ ስሙ ።
አምላክ ፡ ሆይ ፡ አባት ፡ ሁንልን ፡
ጸጋህን ፡ ለጽድቅ ፡ ስጠን ።
አመላችን ፡ ለውጥልን ፡
ቀድስ ፡ ሕይወታችንን ።

O. E.

ሃፀ

Am. 12.

፩ ፡ በመስቀል ፡ ሞተ ፡ መድኃኒቱ ፡
ሊያድነኝ ፡ ብሎ ፡ ከዋሉቱ ፡
ሊመልሰኝም ፡ ከኃጢአቱ ።

ክብር ፡ ለስሙ ።
ክብር ፡ ለስሙ ፡
ክብር ፡ ለስሙ ፡
ነጻ ፡ ስለ ፡ ሰጠኝ ፡ በደሙ ።
ክብር ፡ ለስሙ ።

፪ ፡ በመስቀሉ ፡ ከኃጢአት ፡
ዳንሁኝ ፡
አምላክም ፡ ልጁን ፡ ለወጠልኝ ፡
ከኃጢአት ፡ አርነት ፡ ሊያወጣኝ ።
ክብር ፡ ለስሙ ።
ክብር ፡ ለስሙ ፡

፫ ፡ አቡሩክ ፡ ምንጭ ፡ ከኃጢአት ፡
ያዳነኝ ።
ያ ፡ ምንጭም ፡ አንጽቶ ፡ አጠበኝ ፡
ያማልደኝ ፡ ዘንድም ፡ ተስፋ ፡ አለኝ ።
ክብር ፡ ለስሙ ፡
ክብር ፡ ለስሙ ፡

፬ ፡ ያ ፡ ምንጭም ፡ የሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ነው ፡

ለኃጢአታችን ፡ ሲል ፡ የሞተው ፡
በሰስተኛም ፡ ቀን ፡ የተነሣው ።
ክብር ፡ ለስሙ ።
ክብር ፡ ለስሙ ፡

ግሩ

S. T. 745.

፩ ፤ ያምላክ፡በግ፡ዘመስቀል፡ላይ ፡
የተቀበለውን ፡ ሥቃይ ፡
በምኑት ፡ ስመለከተው ፡
ሕይወትና ፡ ጤና ፡ ነው ።
፪ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የፈሰሰም ፡
ቅዱሱ ፡ የልጁ ፡ ደም ፡
ባምላክ ፡ ፍርድ ፡ አጸደቀኝ ፤
ከክፋቱም ፡ አጠበኝ ።
፫ ፤ ወንበደውም ፡ የጸለየው ፡
ጸሎት ፡ ልመናዬም ፡ ነው ።
አስበኝ ፡ በመንግሥትህ ፤
ስል ፡ የጸጋ ፡ መልስ ፡ ሰጠህ ።

፬ ፤ የሱስ ፡ ካምላክ ፡ ተጥለህ ፡
ፀንጠት ፡ ላይ ፡ ተሰቅለህ ፡
እኔ ፡ ካምላክ ፡ እንዳልጣል ፡
ፍጹም ፡ ተስፋ ፡ ሰጥተሃል ።
፭ ፤ አብ ፡ አውን ፡ ነው ፡ አባቴ ፡
እኔም ፡ በመድኃኒቴ ፡
የሚወደኝ ፡ ልጁ ፡ ነኝ ፡
በቅፉም ፡ ውስጥ ፡ ተቀበለኝ ።

ረስቲን

ግሩ

S.T. 709.

፩ ፤ አዳም፡በውድቀቱ፡ያወረደብን
ሁሉ ፡ በሴት ፡ ዘር ፡ ተፈውስዋል ።
ክርስቶስ ፡ በመስቀሉም ፡ ላይ ፡
ሲሞትልን ፡
ኃጢአታችንን ፡ አርቅዋል ።
በእንጨት ፡ ላይ ፡ የሞት ፡ ሥቃይ ፡
ቅዱሱ ፡ ስለ ፡ ኃጥኣን ፡ ቀምስዋል ።

፱ ፤ ደሜን ፡ ሥጋዬንም ፡ እንኩ ፡
ውሰዱ ።
ይህ ፡ ነው ፡ የኀጢአታችሁ ፡ ስርየት ፡
አለና ፡ ወደ ፡ ሕማም ፡ በመሐዱ ፡
አወረደልን ፡ የአብን ፡ ሥምረት ።
ግሩም ፡ ጭንቁንም ፡ መስቀሉንም ፡
ተሸክሞልን ፡ ዋጀልን ፡ ስርየት ።
፲ ፤ አበሳህም ፡ እንደ ፡ ቅርምዝ ፡
በሆነም ፡
በቅዱስ ፡ ደሙ ፡ ማጥራት ፡ ይችላል።
የሱስ ፡ በመስቀል ፡ ከሞተ ፡ መዳንም ፡
ጽድቅም ፡ ብዕዕናም ፡ ተሰጥቶናል።
የርሱን ፡ ሥቃይ ፡ በምንት ፡ ብታይ ፡
ከሞት ፡ ከመቅሠፍትም ፡ ያድንሃል ።
፲፩ ፤ ግን ፡ የመድኃኒቱን ፡ ደም ፡
የሚንቁ ፡
ፍርድን ፡ ሳይፈሩ ፡ የጸጋን ፡ ብዙት ፡
ችላ ፡ እያሉ ፡ ከየሱስ ፡ ሲርቁ ፡

ምን ፡ ያድናቸው ፡ ይሆን ፡ ከጥፋት ፡
የናቁትን ፡ ፍር ፡ መድኅንን ፡
ግርማውን ፡ ሲለብስ ፡ ያዩታል ፡
በፍርሃት ።
፲፪ ፤ አ ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ በቅዱስ ፡
ሕማምህ ፡
ኀጢአተኞችን ፡ አድነሃል ።
ለመንፈሳችን ፡ ፅረፍት ፡ በድካምህ ፡
እንድትሰጠን ፡ ተጨንቀሃል ።
ሁላችንን ፡ ልታድነን ፡
በቅዱስ ፡ መስቀልህ ፡ ገዝተኸናል።
፲፫ ፤ አንተ ፡ በኀልዎታ ፡ ላይ ፡
የሞትህልን ፡
አ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለማመን ፡
እርዳን ።
የሠራህልንንም ፡ ግለጥልን ፡
እኛም ፡ በመስቀልህ ፡ ኃይል ፡
እንዳን ።

መስቀልህም ፡ ለዘላለም ፡
ተስፋና ፡ ሕይወት ፡ ሊሰጠን ፡
ይብቃን ።

ረዳቱን

ቸኽ

S. T. 194. Am. 164.

፩ ፤ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ቀ·ስሉ ፡
ነፍሴ ፡ ሆይ ፡ ፅረጊ ፡
ወደ ፡ ረጅም ፡ መስቀሉ ፡
አምነሽ ፡ ተጠጊ ።
ያምላክ ፡ ልጅ ፡ እረኛሽም ፡
ሞተ ፡ ለበጎቹ ።
ዕዳን ፡ ሁሉ ፡ ከፈለም ፡
ስለ ፡ ወንድሞቹ ።
፪ ፤ ከምላክ ፡ ፍርድ ፡ ሊጋርደን ፡
ወርቅም ፡ ብርም ፡ ሆነ ፡
ከጥፋት ፡ ሊያድነን ፡
የማይበቃ ፡ ሆነ ።

ነገር ፡ ግን ፡ የአምላክ ፡ ልጅ ፡
መሥዋዕት ፡ ሆነ ፤
እኛንም ፡ ከሰይጣን ፡ እጅ ፡
በሕማሙ ፡ አዳነ ።
፫ ፤ በሕማሙም ፡ ከመንሁ ፡
በርሱ ፡ እድናለሁ ።
ጽድቁን ፡ ከተቀበልሁ ፡
ጻድቅ ፡ እሆናለሁ ።
ንጹሕ ፡ ደሙን ፡ አፍስሶ ፡
ያምላክ ፡ በግ ፡ ሞተልኝ ።
ኃጢአቴን ፡ ደምስሶ ፡
ቅዱስ ፡ እርድ ፡ ሆነልኝ ።
፬ ፤ ደሙም ፡ ስላጸደቀኝ ፡
አብ ፡ ይቀበለኛል ።
የልጁም ፡ ሙ·ሽራ ፡ ነኝ ፡
በርሱም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።
ከእ ፡ ጋር ፡ ተባበረ ፡
ያለም ፡ ፍትወት ፡ ይጥፋ ።

የሱስ ፡ በኔ ፡ ካደረ ፡
የርሱ ፡ ነኝ ፡ በተስፋ ።
፭ ፡ ቀኍለሎቹ ፡ ለሰማይ ፡
ቡሩካን ፡ ደጆች ፡ ናቸው ።
ችጋረኞች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡
ክፍት ፡ በር ፡ አላቸው ።
ለሚታመመውም ፡ ድኃ ፡
ጠበሉ ፡ መነጨ ።
ቅዱስ ፡ የሕይወት ፡ ውኃ ፡
በርሱ ፡ ላይ ፡ ተረጨ ።
፮ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ቀኍለ ፡
ነፍሴ ፡ ሆይ ፡ ዕረፊ ።
ጨናሽ ፡ ነው ፡ በመስቀሉ ፡
ከርሱ ፡ አትራቂ ።
በዚህ ፡ ቅዱስ ፡ አምባ ፡ ላይ ፡
ሕይወት ፡ ታገኛለሽ ።
ከፍርሃትና ፡ ሥቃይ ፡
በርሱ ፡ ትድኛለሽ ።

ረስቱን ።

ትንሣኤው ።

ቁጽ

S. T. 208.

፩ ፡ ክርስቶስ ፡ ሕያው ፡ ሆነ ፡
መቃብር ፡ በራ ፡
መድኃኒት ፡ ተገኘ ፡ ትንቢትም ፡ መላ ።
ግርማን ፡ ተጐናጽፎ ፡ ከሞት ፡
ወጥትዋል ፡
ከጠላት ፡ ተዋጋ ፡ ድል ፡ ግን ፡
ነሥትዋል ።
፪ ፡ ማኅተም ፡ ተፈታ ፡ ድንጋይ ፡ ለቀቀ ፡
ጠባቂው ፡ ፈርቶ ፡ ፈጥኖ ፡ ሸሸ ፡
ሲኦልም ፡ ተገዛ ። ሃሌ ፡ ሉያ ።
፫ ፡ ከጨለማ ፡ ጋራ ፡ ብርሃን ፡ ሲዋጋ ፡
ብርሃን ፡ ለዘላለም ፡ ሽሮ ፡ ድል ፡ ነሣ ።
ያ ፡ ሞት ፡ ትደበየ ፡ ድል ፡ ነሣ ፡
ሕይወት ፡
ተስፋችን ፡ በረታ ፡ ለማበት ፡ እምነት ።

እናንት ፡ ኀዘነተኞች ፡ ክልብ ፡ ተቀኙ ።
ከሞት ፡ አዳነን ፡ በየውሀቱ ፤
ሊኖር ፡ ከኛ ፡ ጋራ ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

፫ ፡ ሰማይ ፡ ከምድራችን ፡ አሁን ፡
ታርቅዋል ።
መቃብር ፡ የደስታ ፡ መንገድ ፡ ሆንዋል ።
እንባን ፡ ያቅረራችሁ ፡ በመስቀል ፡
ትይዩ ፤
ጠላቶች ፡ ቢቆጩ ፡ ሐሜት ፡ አድርገ ።
የጠፉትን ፡ ወዶ ፡ በጎ ፡ እረኛ ፡
ገና ፡ ይጠራል ፡ ክርሱ ፡ የከዳ ፡
ይመለስ ፡ ለመንጋ ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

፬ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸናች ፡
ነፋሳት ፡ ይምጡ ፡
በብርሃኑ ፡ ፍጥነት ፡ ሰፋ ፡ ትምህርቱ ፡
በዓለሙ ፡ ወጡ ፡ መልእክተኞቹ ፡
ሞት ፡ እንኳ ፡ ሳይፈሩ ፡ ወንጌል ፡
ሰበኩ ።

ስለኛ ፡ ለሞተ ፡ ነጻ ፡ ላወጣን ፡
ምስክር ፡ ሊሰጡ ፤ ሰውን ፡ ለማዳን ፡
ሊጣሩ ፡ በደስታ ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

፭ ፤ ለምን ፡ አልቅሳችሁ ፡
እናንት ፡ ምእመናን ፤
ስንት ፡ አጭር ፡ ነው ፡ ዘመን ፡ ሞት ፡
እስኪጠራን ።
መሬት ፡ እንደ ፡ እናት ፡ ልታቅፋችሁ ፤
እንደ ፡ ሕያው ፡ ዘር ፡ ቶሎ ፡ ልትወጡ ።
የዘራው ፡ ይመጣል ፡ በመከር ፡ ጊዜ ፤
ክርዳድን ፡ ይለያል ፡ ከጥሩ ፡ ፍሬ ፡
ስንዴን ፡ ሊያገባ ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

O. E.
Ins. 383
3/2
Jesus Calls Us
S. S. 762

፺፬ Am. 107. S. T. 211.

፮ ፡ በአፋችሁ ፡ ከልባችሁ ፡
ክርስቶስን ፡ አመስግኑ ።
ስለ ፡ እኛ ፡ ሞተ ፡ ተኛ ፡

ሶስት ፡ ቀን ፡ በመቃብሩ ።
ከመቃብርም ፡ በክብር ፡
ተነሣ ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

፱ ፡ የኛን ፡ ሥራ ፡ እርሱ ፡ ሠራ ፡
ለኛ ፡ ጽድቅ ፡ ይሰጠናል ።
ኃጢአታችን ፡ ችግራችን ፡
አሁን ፡ ፍጹም ፡ ጠፍትዋል ።
በሞት ፡ ፈንታ ፡ ሕይወት ፡ ደስታ ፡
ሰጠን ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

፲ ፡ ልንፈታ ፡ እርሱ ፡ መጣ ፡
ያለም ፡ ቤዛ ፡ እርሱ ፡ ነው ።
አሁን ፡ ሰይጣን ፡ ኃይሉን ፡ አጣ ፡
ኃይልም ፡ ሁሉ ፡ ለልጅ ፡ ነው ።
አሁን ፡ እኛን ፡ ኃጢአተኞች ፡
አዳነን ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

፲፩ ፡ እናንት ፡ ሁሉ ፡ በድምፅ ፡ ሙሉ ፡
አምላክን ፡ አመስግኑ ።
ለልጅ ፡ ደግሞ ፡ ክብርን ፡ ስጡ ፡

ስለታላቅ ፡ ምሕረቱ ።
ለሚቀድስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ዘምሩ ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

ልንዳል ።

፮

ልዩ ፡ ዜማ ፡ ፮ ።

፩ ፡ ጌታ ፡ ከሞት ፡ ተነሥትዋል ፡
መቃብር ፡ አሁን ፡ በረ ።
የሞትን ፡ ኃይል ፡ አሸንፍዋል ፡
ሕይወትንም ፡ አሰፋ ።
ከመቃብር ፡ ይወጣል ፡
በወንጌሉ ፡ ተጽፍዋል ፡
ትንሣኤ ፡ ነኝ ፡ ሕይወትም ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

፪ ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ አካሔዴን ፡
በርሱ ፡ ተስፋ ፡ ላቀና ።
ልነሣ ፡ ነኝ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ።
ልኖር ፡ ለርሱ ፡ ምስጋና ፡
በማይጠፋብኝ ፡ ሕይወት ፡

ከንቱነት ፡ የማይነካበት ፡
በኃጢአት ፡ የማይረክስ ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

፫ ፤ ሞት ፡ ሆይ ፡ የታለ ፡ ያንተ ፡ ሾህ ፤
ማሸነፍህ ፡ የታለ ፤
የሱስ ፡ ፍጹም ፡ ከሸነፈህ ፡
የሚገዳኝ ፡ ማን ፡ አለ ፤
ለዘላለም ፡ የርሱ ፡ ነኝ ።
ይላል ፡ እኔ ፡ ወዳልሁኝ ፡
እናንትም ፡ ልትሆኑ ። ሃሴ ፡ ሉያ ።

ሉንዳል ። — O. E.

Praise God
From Whom All
Blessings Flow
Ins. cover

፷፩

S. T. 153. Am.100

፩ ፤ የደስታ ፡ ዘመን ፡ ሁንዋል ፤
ክርስቶስ ፡ አሁን ፡ ድል ፡ ነሥትዋል ።
ሲነግም ፡ ከመቃብሩ ፡
ታየልን ፡ አምላክነቱ ።

፪ ፤ ከመቅሠፍትም ፡ ሊያድነን ፡
በሞተ ፡ በሶስተኛው ፡ ቀን ፡

ተነሥቶ ፡ ደግሞ ፡ እንዲያርግ ፡
ተጽፎ ፡ ነበር ፡ በምላክ ፡ ሕግ ።

፫ ፤ ቢጠብቁም ፡ መቃብሩን ፡
ወጣበት ፡ ጥሶ ፡ ድንጋዩን ።
የሕይወት ፡ ንጉሥም ፡ ቢሞት ፡
አልቀረም ፡ በሲያል ፡ ግዙት ።

፬ ፤ ሲያል ፡ አሁን ፡ ተሸነፈ ፤
የሞትም ፡ ግፍ ፡ ተቀሠፈ ።
ሃሴ ፡ ሉያ ። ተነሥትዋል ፡
ጌታችን ፡ እንደ ፡ ተስፋው ፡ ቃል ።

፭ ፤ ከሞት ፡ ሥልጣን ፡ ያወጣኸን ፤
አ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፤ ተመስገን ።
ጻድቃን ፡ በሚነሡበት ፡ ቀን ፡
የሕይወት ፡ ትንሣኤ ፡ ስጠን ።

ረስቲን ።

፷፪

S. T. 90. Am. 13.

፩ ፤ ድል ፡ ነሥተሃል ፡ አ ፡ የሱስ ፤
ዕርቃችን ፡ አንተ ፡ ነህ ።

ላንተ ፡ ለሕይወት ፡ ንጉሥ ፡
ምስጋና ፡ እንስጥህ ።
የሞትን ፡ ኃይል ፡ ከሰበርክ ፡
ለእኛ ፡ ሕይወት ፡ ፈጠርክ ፡
በቅዱስ ፡ ትንሣኤህ ።
፪ ፡ መሬቱ ፡ ቤትህ ፡ ነበር ፡
ለኛም ፡ ይከፈታል ።
እኛንም ፡ ከመቃብር ፡
ድምጽህ ፡ ያስነሣናል ።
አንተንም ፡ በሕይወቱ ፡
የወደደህ ፡ በሞቱ ፡
በዕቅፍህ ፡ ውስጥ ፡ ያርፋል ።
፫ ፡ ኋላኛውም ፡ ቀን ፡ ሲነጋ ፡
በግርማህ ፡ ስትታይ ፡
ዙፋንህ ፡ ሲዘረጋ ፡
ለፍርድ ፡ በአሕዛብ ፡ ላይ ፡
መለከቱም ፡ ሲሰማ ፡
ሕይወቱ ፡ እንደለማ ፡
ድምጽህ ፡ ያስታውቃል ።

Une. 121 Low in the Grove S.S. 152

Am. 184.

፩ ፡ በመቃብር ፡ ተኛ ፡ የዓለም ፡
መድኅን ፡
ከዚያም ፡ ወጣ ፡ ለኛ ፡ መድኃኒታችን ።
ከመቃብር ፡ ተነሣ ፡
ድል ፡ ነሥቶልን ፡ በጠላቱ ፡ ላይ ፡
ተነሣ ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ለኛ ፡ ተነሣ ፡
ለዘላለም ፡ ሊነግሥልን ፡ በሰማይ ፡
ተነሣ ፡ ተነሣ ፡ ድል ፡ ነሥቶልን ፡ ተነሣ ።
፪ ፡ በክንቱ ፡ ጠበቁት ፡ የርሱን ፡
መቃብር ፡
በክንቱም ፡ አተሙት ፡ የሕንፃን ፡ በር ።
ከመቃብር ፡ . . . . ።
፫ ፡ ሞትን ፡ አሸነፈ ፡ የዓለም ፡
መድኅን ፡
ሕንፃን ፡ ፈነቀለ ፡ መድኃኒታችን ።
ከመቃብር ፡ . . . . ።

Christ the Lord is Risen Today
S. S. 158
Ine. 122

፺፱

Am. 185.

፩ ፤ ክርስቶስ ፡ ዛሬ ፡ ተነሥትዋል ።
ሃሌ ፡ ሉያ ።
ቅዱስ ፡ ቀናችን ፡ ነግትዋል ።
ሃሌ ፡ ሉያ ።
በመስቀል ፡ የሞተልን ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።
ዕዳችንን ፡ ሊያስወግድልን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ።
፪ ፤ ለክርስቶስ ፡ ንጉሠ ፡ ስብሐት ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ።
ሙዳሴን ፡ እናቅርብለት ።
ሃሌ ፡ ሉያ ።
በመቃብር ፡ ለተኛ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።
ሕይወት ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ለኃጢአተኛ ።
ሃሌ ፡ ሉያ ።
፫ ፤ በሥቃዩ ፡ አዳነን ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።
መድኃኒትም ፡ ሆነልን ። ሃሌ ፡ ሉያ ።

አሁን ፡ በላይ ፡ ነግሥዋል ።
ሃሌ ፡ ሉያ ።
መላእክትም ፡ በዙሪያው ፡ ቁመዋል ።
ሃሌ ፡ ሉያ ።
፬ ፤ ምስጋና ፡ ለአምላካችን ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ።
እናቅርብ ፡ ከልባችን ። ሃሌ ፡ ሉያ ።
ዓለም ፡ ምሉ ፡ ይቀደስ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ።
ለአብ ፡ ለወልድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ሃሌ ፡ ሉያ ።

በዓለ ፡ ኀምሳ ።

፻

Am. 188.

፩ ፤ አምላክ ፡ የኔ ፡ አረኛ ፡ ነው ፡
የሚያሳጣኝ ፡ የለም ።
ወደ ፡ ለመለመ ፡ መስክ ፡
እርሱ ፡ ይመራኛል ።

ይመራኛል ፡ ይመራኛል ፡
ወደ ፡ ጥሩ ፡ ውኃ ፡ በለመለመ ፡ .
መስክ ፡ ይመራኛል ።
፪ ፡ ደክማ ፡ ነፍሴን ፡ ያሳርፋል ፡
በጽድቅ ፡ መንገድ ፡ ይመራል ፤
የልዑል ፡ ክንድ ፡ ያጸናኛል ፡
በስሙ ፡ ምክንያት ።
ይመራኛል ፡ . . . . . ።
፫ ፡ በሞት ፡ ጽላ ፡ ወንዝ ፡ ብሔድ ፡
ምንም ፡ ክፉን ፡ አልፈራም ፤
አንተ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ከሆንህ ፡
ጽናቴም ፡ ምርኩዝህ ።
ይመራኛል ፡ . . . . . ።
፬ ፡ ገበታዬን ፡ አዘጋጀህ ፡
በጸላቶቼ ፡ ፊት ፤
ራሴን ፡ በዘይት ፡ ቀባኸው ፡
ጽዋዬም ፡ ተርፍዋል ።
ይመራኛል ፡ . . . . ።

፭ ፡ ያንተ ፡ ምሕረት ፡ ቸርነትም ፡
እኔን ፡ ይከተላሉ ።
ለዘላለም ፡ እኖራለሁ ፡
በልዑል ፡ አምላክ ቤት ።
ይመራኛል ፡ . . . . ።

Iva. 384 ፻፸ What a Friend We Have
S. S. 319
S. T. 447. Am. 139.

፩ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የኔ ፡ ወዳጅ ፡
እንደእርሱ ፡ የለኝም ።
ሌሎችም ፡ እንኳ ፡ ቢለዩኝ ፡
እርሱ ፡ ግን ፡ አያደርገውም ።
ማነው ፡ አውን ፡ የሚለየኝ ፡
ጌታዬ ፡ ከወደደኝ ፡
አንድነት ፡ ከእርሱ ፡ አለኝ ፡
ማንም ፡ የማይወስድብኝ ።
፪ ፡ እርሱ ፡ ሞተ ፡ ስለ ፡ እኔ ፡
ማነው ፡ የሚፈርድብኝ ፡
ከአባቴ ፡ ለመነልኝ ፡

ለዘላለም ፡ ጠቀመኝ ።
ማነው ፡ አሁን ፡ የሚከሰኝ ፤
እርሱ ፡ ራሱ ፡ መረጠኝ ።
ማነው ፡ ከርሱ ፡ የሚነጥቀኝ ፡
ጌታዬ ፡ ሲጠብቀኝ ፤
፫ ፡ ፍጹም ፡ ተስፋ ፡ አሁን ፡ አለኝ ።
ሞትም ፡ ሆነ ፡ ሕይወትም ፡
ከጌታዬ ፡ አይለየኝም ፡
ራብም ፡ ሆነ ፡ ጭንቀትም ፤
ዝቅታም ፡ ከፍታም ፡ ጓዘን ፡ ችግር ፡
አላፊም ፡ መጭም ፡ ቢሆን ፡
ከዚህ ፡ ፍቅር ፡ አይለየኝም ፡
በየሰዓት ፡ ያገኘሁት ።

ሉንዳል ።

፻፺፯

S. T. 348.

፩ ፡ አንድ ፡ ወዳጅ ፡
በምሔድበት ፡ ሁሉ ፡
ከኔ ፡ ጋራ ፡ ይመላለሳል ።

ላይኔ ፡ አይታይም ፡ ግን ፡ ቅዱስ ፡ ቃሉ ፡
ወደ ፡ ልቤ ፡ ይደርስልኛል ።
፪ ፡ ወዳጅ ፡ ስለኔ ፡ ሙቶ ፡ ነበር ፡
ከመታሰር ፡ ግን ፡ ተነሥትዋል ።
እረኛችን ፡ ሁሌ ፡ በማይነገር ፡
ርኅራኄ ፡ ለመንጋው ፡ ያስባል ።
፫ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚያስፈልገኝን ፡
ቸር ፡ እረኛ ፡ ያቀርብልኛል ።
ልቤንም ፡ የሚያቄስለኝን ፡
ፈውሶ ፡ ረድኤት ፡ ይሰጠኛል ።
አጭር ፡ ዘመን ፡ እንዲሰወርብኝ ፡
እርሱ ፡ ራሱ ፡ ገልጦ ፡ ብሎኛል ፤
ግን ፡ ተመልሶ ፡ ሲገለጥልኝ ፡
ደስታና ፡ ሰላም ፡ ይሆነኛል ።
፬ ፡ ድኅነኛ ፡ እሙኑ ፡ መድኃኒት ፡
ቶማስ ፡ ሲጠረጥር ፡ አሰበው ፡
እንዲሰጠውም ፡ ቅዱስ ፡ መጸናናት ፡
ቍስሎቹን ፡ አመለከተው ።

ዶማስ ፡ ጌታን ፡ አውቆ ፡ አዲስ ፡ ተስፋ ፡
ምሉ ፡ እምነትም ፡ ተቀብሎ ፡
ጮኸ ፡ በማይነገር ፡ ቅዱስ ፡ ደስታ ፡
ጌታዬና ፡ አምላኬ ፡ ብሎ ።
፱ ፡ ለኔ ፡ ደግሞ ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡
ራራልኝ ፡
ያንን ፡ ደስታ ፡ አትከልክለኝ ።
አለማመኔም ፡ እንዲጠፋልኝ ፡
ቁስሎችህን ፡ አሳስበኝ ።
ቸር ፡ አረኛ ፡ እኔ ፡ ምስኪን ፡ በግህ ፡
ተስፋዬ ፡ በአንተ ፡ ብቻ ፡ ነው ።
አንተንም ፡ አ ፡ አምላኬ ፡ የማውቅህ ፡
ቁስልህን ፡ ስታሳየኝ ፡ ነው ።
፲ ፡ የተወጋው ፡ ልብህ ፡
አ ፡ ቸር ፡ መድኅን ፡
ያስበኝ ፡ በዓለም ፡ በረሃ ።
በምንትም ፡ ልመልከት ፡ ቁስልህን ፡
በትካዜና ፡ በፍሥሓ ።

ና ፡ አሳርፈኝ ፡ በርኅሩኅ ፡ ዕቅፍህ ፡
አድርሰኝ ፡ ወደየሩሳሌም ።
ድኜም ፡ ፊት ፡ ዶፊት ፡ አ ፡ ጌታ ፡ ልይህ ፡
አ ፡ መድኃኒቴ ፡ አ ፡ አምላኬም ።
ረዳቴን ።

Free From the Law
Rev. 112

ፀፀ

S. T. 304. Am. 85.

፩ ፡ ዕዳ ፡ ተከፍሎ ፡ ድልም ፡ ተሰጠ ፡
መድኃኒታችን ፡ ሞተ ፡ ስለኛ ።
ከአሪት ፡ መርገም ፡ ከኃጢአት ፡
ክርስቶስ ፡ አዳነን ፡ ሁላችን ።
አሁን ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ ይህን ፡
ነገር ፡ እመን ፡
ክርስቶስ ፡ ሲሞት ፡ ተገዛን ፡ ሁላችን ፡
አሁን ፡ ተቀበለውና ፡ ዳን ።
በደሙ ፡ ገዛን ፡ ሁላችን ።
፪ ፡ አርነት ፡ ወጣን ፡ ፍርድ ፡
የለብንም ፡

ሕሊናችንም ፡ አይነቅፈንም ።
ኑ ፡ ወደ ፡ እኔ ፡ የሱስ ፡ ይላል ፡
እርሱ ፡ አዳነን ፡ ሁላችን ።
አሁን ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ . . . ።
ቮ ፡ ምንኛ፡ታላቅ፡የአምላክ፡ጸጋ ፡
ልጆቹ ፡ ነን ፡ የሚሉት ፡ ብሌን ።
እንደዚህ ፡ ፍቅር ፡ ይገኛልን ፡
ክርስቶስ ፡ አዳነን ፡ ሁላችን ።
አሁን ፡ ሰው ፡ ሆይ ፡ . . . ።

ሶንዳል ።

He Leadeth Me
S.S. 542
Num. 71

ጀህ

Am. 114. S. T.667

፩ ፡ ይመራኛል ፡ ይመራኛል ፡
እንዴት ፡ ያለው ፡ መጽናናት ።
በሐዲሁበት ፡ ባለሁበት ፡
የአምላክ ፡ እጅ ፡ ይመራኛል ።
ይመራኛል ፡ ይመራኛል ፡
በገዛ ፡ እጁ ፡ ይመራኛል ።

ተከታዩ ፡ እሆናለሁ ፡
በእርሱ ፡ እጅ ፡ ከተመራሁ ።
፪ ጌታ ፡ ሆይ ፡ እኔን ፡ እርዳኝ ፡
ከማጉረምረምም ፡ ጠብቅኝ ።
በፈተናም ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡
አምላኬ ፡ ሆይ ፡ እኔን ፡ እርዳኝ ።
ይመራኛል ፡ . . . ።
ቮ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ስትመራኝ፡
በጸጋህ ፡ ከገኘሁ ፡ ሁሉን ፡
አልፈራውም ፡ የሞትን ፡ ጽላ ፡
በዮርዳኖስ ፡ ካሻገርኸኝ ።
ይመራኛል ፡ . . . ።

Jesus Savior Pilot Me
Num. 64 S. T. 184 S.S. 556

፩ ፡ የሱስ ፡ ያስፈልገኛል ፡
በደሴን ፡ ይቅር ፡ ይላል ፡
ጋሻም ፡ ይሆንልኛል ።
እርሱ ፡ ብቻ ፡ ያድነኛል ፡
ፍቅሩም ፡ ሕይወት ፡ ነው ፡ ለኔ ።
የሱስ ፡ ነው ፡ መድኃኒቱ ።

፪ ፤ ያለ ፡ የሱስ ፡ ተስፋም ፡ የለኝ፡
ያለ ፡ የሱስ ፡ ምሕረትም ፡
ምንም ፡ አይሆንልኝም ።
የሱስ ፡ እምነትን ፡ ካልሰጠኝ ፡
አላገኝም ፡ ለፍቼ ።
የሱስ ፡ ነው ፡ መድኃኒቱ ።

፫ ፤ ስለዚህ ፡ ወዳንተ ፡ የሱስ ፡
እመጣለሁ ፡ ለምኜ ፡
ጸጋህን ፡ ተማጥኜ ።
እውነተኛውን ፡ ሕይወት ፡ ለኩስ ፡
በተሰበረው ፡ ልቤ ።
አንተ ፡ ነህ ፡ መድኃኒቱ ።

ረስቲን ።

ፎፅ

Am. 11. S. T. 525.

፩ ፤ የሱስ፡ በሚመራኝ፡ መንገድ፡
ምንድር ፡ ያስጠይቀኛል ፤

ምሕረቱንም ፡ ይሰጠኛል ፡
ሁልጊዜም ፡ ይመራኛል ።
ሰላሙን ፡ ያካፍለኛል ፡ አምኜ ፡
እንድኖርበት ።
ከሚመጣብኝም ፡ ሁሉ ፡
የሱስ ፡ ይጠብቀኛል ።
ከሚመጣብኝም ፡ ሁሉ ፡
የሱስ ፡ ይጠብቀኛል ።

፪ ፤ የሱስ ፡ የሚመራኝ፡መንገድ፡
እጅጉን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።
ጸጋውንም ፡ ይሰጠኛል ፤
ሕያው ፡ ምግብ ፡ ይሰጠኛል ።
ከድካሜ ፡ እንዲያጸናኝ ፡
ነፍሴም ፡ እንዳትጸማ ።
መንፈሱም ፡ ይፈልቅልኛል ፡
በደስታም ፡ ያጠጣኛል ።
መንፈሱም ፡ ይፈልቅልኛል ፡
በደስታም ፡ ያጠጣኛል ።